20ኛ ዓመት ቁጥር 1
**20th** Year No. 1

ባሕር ዳር ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ.ም
Bahir Dar, November 07, 2014

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት
# ዝክረ ሕግ
# ZIKRE HIG
## Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

**Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State**

✉ *1324*
ያንዱ ዋጋ 37 ብር
Unit Price Birr 37

| ማውጫ | Content |
|---|---|
| **አዋጅ ቁጥር 220/2007 ዓ.ም** | **Proclamation No 220/2014** |
| **የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኅብረት ሥራ ማኅበራትን ለማቋቋም ተሻሽሎ የወጣ አዋጅ** | **The Amhara National Regional State Revised Cooperative Societies Establishment Proclamation** |

## አዋጅ ቁጥር 220 /2007 ዓ.ም

### በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለው የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማቋቋሚያ አዋጅ

## Proclamation No.220/2014

**A Proclamation Issued to Provide for the Establishment of Cooperatice Societies of the Amhara National Regional State**

የኅብረት ሥራ ማኅበራት በኅብረተሰቡ ውስጥ የተበታተነውን የፋይናንስ፣ የማቴሪያልና የሰው ኃይል ሃብት በማሰባሰብና በማንቀሳቀስ ከፍተኛ ልማት የሚፈጥሩ ተቋማት መሆናቸው በመታመኑ፤

**WHEREAS**, it is believed that cooperative societies are institutions that create the highest development in the society by collecting and mobilizing the scattered finance, material and manpower resources.

መንግስት ያወጣቸውን የተለያዩ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች በመፈፀም ሂደት የኅብረት ስራ ማኅበራት ከፍተኛ ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ መሆኑ አሳማኝ ሆኖ በመገኘቱ፤

**WHEREAS**, it has been convincing that cooperative societies play the highest role in the process of implementing of different developmental policies and strategies issued by the Government.

አባላት የሚፈልጉት ግብዓትና የኢንዱስትሪ ውጤት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብላቸውና የምርት ውጤታቸውም ሆነ አገልግሎታቸው በአገር ውስጥና በውጭ ሀገር የተሻለ ዋጋ እንዲገኝላቸው ለማድረግ የኅብረት ስራ ማኅበራት ሚና ተተኪ የሌለው በመሆኑ፤

WHEREAS, the role of cooperative societies are unsubstituable to cause to submit the needed input and industry product in reasonable price to members and to have their product as well as services better price in domestic and foreign market;

የኅብረት ስራ ማኅበራት በነጻ ገበያው ስርዓት ውስጥ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it has become necessary to enable cooperative societies to play the appropriate role in the free market economic system.

የኅብረት ስራ ማህበራት መሠረታዊ መርሆዎችን ተከትለው በአባሎቻቸው ሙሉ ፈቃደኝነትና ዲሞክራሲዊ አመራር ተደራጅተው የአባሎቻቸውን ጥቅም እንዲያስከብሩና በብሄራዊ የኢኮኖሚ ልማት ውስጥ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ይህ የተሻሻለው አዋጅ ሰፊ እድል የሚፈጥር ሆኖ በመገኘቱ፤

WHERE AS, it has been found necessary that,this revised proclamation shall create a greate opportunity for cooperative societies to play an appropriate role in the development of national economy and nurture their members use, following the principles of cooperative societies, established with their members full volunterism and democratic leadership;

በነበረው አዋጅ ያልተካተቱና አፈፃፀም ላይ ችግር እየሆኑ ያሉ ጉዳዮችን በማካተት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል በግልጽ አዋጅ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

WHERE AS, it is necessary to stipulate proclamation clearly, that enable to prevent and control corruption and incorrect work procedure, by incorporating the un-included in the previous proclamation and issues that create problem for performance of activities;

በአጠቃላይ ይህንን ለማሳካት የኅብረት ስራ ማህበራት የሚደራጁበትንና የሚተዳደሩበትን የተሻሻለና የተሟላ ህግ ማውጣት በማስፈለጉ ፤

WHERE AS, it has become necessary to issue a comprehensive legislation by which cooperative societies are organized and managed in order to achieve generally the above mentioned objectives;

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ /49/ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ድንጋጌ መሰረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

NOW,THEREFORE, in accordance with the provision of Article 49 sub-Article 3(1) of the Revised constitution of the National Region it is hereby proclaimed as follows:

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የተሻሻለዉ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 220/2007 ዓ/ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል"፡፡

1. **Short Title**

   This Proclamation may be cited as "the Revised Establishment of Cooperative Societies Proclamation No. 220/2014."

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. 'ማኅበር' ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የተደራጀና የተመዘገበ የኅብረት ሥራ ማኅበር ሲሆን ፣ በተለይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትንና የመሳሰሉትን ይጨምራል፡-
      - ሀ. የገበሬዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት፤
      - ለ. የመኖሪያ ቤት የኅብረት ሥራ ማኅበራት፤
      - ሐ. የኢንዱስትሪና የዕደ ጥበብ የኅብረት ሥራ ማኅበራት፤
      - መ. የሸማቾች ኅብረት ሥራ ማኅበራት፤
      - ሠ. የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት፤
      - ረ. የዓሣ አስጋሪዎች የኅብረት ሥራ ማኅበራት፤
      - ሰ.የማዕድን የኅብረት ሥራ ማኅበራት፡፡

2. **Definitions**

   Unless the context otherwise requires; in this proclamation:

   1. "Society" means cooperative society which is established and registered in accordance with this proclamation and it shall in particular include the following:
      - a. Agricultural cooperative societies;
      - b. Housing cooperative societies;
      - c. Industrial and Artisans producer's cooperative societies;
      - d. Consumers cooperative societies;
      - e. Savings and credit cooperative societies;
      - f. Fishery cooperative socities;
      - g. Mining cooperative societies.

2. “የኅብረት ሥራ ማኅበር” ማለት ሰዎች በፍቃደኝነት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮቻቸውን በጋራ ለመፍታት የሚያቋቁሙትና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚያስተዳድሩት ድርጅት ነው፤
3. “አባል” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የአባልነት መመዘኛዎችን አሟልቶ የተመዘገበ ማንኛውም ግለሰብ ወይም የተቋቋመ ማኅበር ነው፤
4. “ጠቅላላ ጉባኤ“ ማለት የአንድ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበር ጠቅላላ አባላት ወይም በከፍተኛ ደረጃ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ተወካዮች የሚገኙበት ጉባኤ ነው፤
5. “ልዩ ውሳኔ” ማለት በአባላቱ ላይ አስገዳጅነት እንዲኖረው ከአንድ ማኅበር አባላት ውስጥ በሁለት ሶስተኛው መጽደቅ ያለበት ውሳኔ ነው፤
6. “የሥራ አመራር ኮሚቴ“ ማለት በአንድ መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ ተመርጦ መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበሩን እንዲመራ ኃላፊነት የተጣለበት አካል ነው፤
7. “የሥራ አመራር ቦርድ” ማለት በአንድ ከፍተኛ ደረጃ የኅብረት ሥራ ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ ተመርጦ የከፍተኛ ደረጃ የኅብረት ሥራ ማኅበሩን ሥራዎች በበላይ ሆኖ እንዲመራ ኃላፊነት የተጣለበት አካል ነው፤

2. “Cooperative society” means a society established by individual on voluntary basis to collectively solve their economic and social problem and to democratically manage same;
3. “Member” means any physical person, or society established under this proclamation which is registered after fulfilling his membership obligations.
4. “General Assembly” means an assembly, a meeting of members of a primary cooperative society or representatives of the highest level of cooperative societies.
5. “Especial resolution” means a resolution passed by a two third majority of the members to be binding on all members.
6. “Management committee” means a body elected and empowered by the general assembly of the primary cooperative society with the responsibility to manage the activities of same.
7. “Board of management” means a body elected and empowered by the general assembly of the highest level cooperative society with the responsiblilty to manage the works.

8. “አግባብ ያለው ባለሥልጣን” ማለት የኅብረት ሥራ ማኅበራት ኤጀንሲ ሲሆን በዚህ አዋጅ አግባብ ያለው ባለስልጣን እየተባለ ሊጠራ ይችላል፤

9. “ዩኒዬን” ማለት ከአንድ በላይ የሆኑ ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያቋቁሙት ድርጅት ነው፤

10. “ፌዴሬሽን” ማለት ከአንድ በላይ የሆኑና ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው ዩኒዬኖች ስብስብ ነው፤

11. “የሥራ ክልል” ማለት በማኅበሩ ሥራ በትጋት ለመሳተፍ የሚያስችል የአባላት አሰፋፈርና አላማቸውን ተግባራዊ ለማድረግ ማኅበሩ ለመነሻነት የሚንቀሳቀስበት አካባቢ ነው፤

12. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

## 3. የፆታ አገላለጽ

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለፀው ሁሉ ለሴት ፆታም እኩል ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. የማኅበራት ዓላማዎች፣

በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ ማኅበር ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት አንዱ ወይም ከአንድ በላይ ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

1. አባላት በተናጠል በመሥራት ሊወጧቸው የማይችሏቸውን ችግሮች በጋራ መፍታት፤
2. አባላት ያላቸውን ዕውቀት፣ ሀብትና ጉልበት በማቀናጀት የተሻለ ውጤት ማግኘት ፤

8. “Appropriate Authority” means an organ established for the purpose to organize, to register, to give training, to conduct research and provide other technical assistance to cooperative societies and include other subordinate bodies.

9. “Union” means an enterprise established by more than one primary cooperative societies having similar objective.

10. “Federation” means a collection of unions of more than one and having similar objective.

11. “Working Region” means settlement of members that enable to participate diligently in the work of the society and the initial surroundings of the society to implement their objective.

12. “Person” means a natural or juridical person.

## 3. Gender

Provisions of the proclamation set out in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

## 4. Objectives of the Society

The society established under this proclamation shall have one or more of the following objectives:

1. To solve problems collectively which members can not individually achieve;
2. To achieve a better result by coordinating their knowledge, wealth and labor;

3. በራስ መተማመንን ማጐልበት፤

4. ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ችግሮችን በተባበረ ጥረት መከላከል ፣ መቋቋምና ማስወገድ፤

5.ለማምረት የሚያስፈልገውን ወጪና የአገልግሎት ዋጋን ለመቀነስ ፣ አባላት የሚፈልጉትን ግብዓት ወይም አገልግሎት በአነስተኛ ዋጋ እንዲያገኙና ምርታቸው ወይም አገልግሎታቸው የተሻለ የገበያ ዋጋ እንዲያገኝ ማድረግ፤

6.የቴክኒክ ዕውቀትን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉ ዘዴዎች እንዲስፋፉ ማድረግ፣

7.የቁጠባና ብድር አገልግሎት እንዲዳብርና እንዲስፋፉ ማድረግ፤

8.አባላት በግላቸው ቢሰሩ ኖሮ ሊደርስባቸው የሚችለውን ጉዳትና ኪሳራ በጋራ በመካፈል የእያንዳንዱን ሰው ጉዳትና ኪሣራ መቀነስ፤

9.አባላትንና የአካባቢውን ህብረተሰብ በማስተማርና በማሰልጠን ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ባህልን ማጐልበት፡፡

## 5. ማኀበራት የሚመሩባቸው መርሆዎች፣

1. የኀብረት ሥራ ማኀበራት አባልነት በማኀበራቱ አገልግሎት ለመጠቀም ለሚፈልጉና የአባልነት ግዴታዎችን ለመቀበል ፍቃደኛ ለሆኑ ሰዎች ሁሉ በጾታ ፣ በማኀበራዊ አቋም ፣ በዘር ፣ በፖለቲካ አመለካከት ፣ ወይም በሀይማኖት ልዩነት ሳይደረግ ለሁሉም ክፍት ይሆናል፤



3.To promote self-reliance;

4.To collectively protect, withstanding and solve economic problems;

5. To improve the living standards of members by reducing the required expenses for production and service costs by providing input or service at a minimum cost or by finding a better price to their products or services;

6.To expand the mechanism by which technical knowledge could be put in to practice;

7.To develop and promote savings and credit services;

8.To minimize and reduce the individual impact of risks and uncertainties, dividing together;

9.To develop the social and economic culture of the members and the surrounding community through education and training.

## 5. Guiding Principles of Cooperative Societies

1. Cooperative societies are voluntary organizations open to all persons able to use their services and willing to accept the responsibilities of membership without gender, social, racial, political or religious discrimination.

2. ማኅበራት ፖሊሲ በማውጣትና ውሳኔዎችን በማሳለፍ የነቃ ተሳትፎ በሚያደርጉ አባላት የሚመሩ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች ናቸው፡፡ እያንዳንዱ አባል እኩል ድምፅ ያለው ሲሆን አንድ አባል አንድ ድምፅ ብቻ ይኖረዋል፤

3. ከትርፍ ለመጠባበቂያና ለሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች ተቀንሶ እና እንዲቀመጥ ተደርጎ ለማኅበሩ ባደረጉት አስተዋፅኦና ተሳትፎ መጠን ለአባላት ይከፋፈላል፤

4. ማኅበራት ከሌሎች አካላት ጋር ስምምነት የሚያደርጉት ወይም ከማኅበራቸው ውጪ ከሚገኝ ምንጭ ገንዘብ መበደር የሚችሉት የአባላትን ዲሞክራሲያዊ ቁጥጥር በሚያረጋግጥና የማኅበራቸውን የራስ አገዝ ባህሪውን በማይነካ ሁኔታ መሆን ይኖርበታል፤

5. ማኅበራት አባሎቻቸው ፣ ተመራጮቻቸው ፣ ሥራ አስኪያጆቻቸውና ሠራተኞቻቸው ለየማኅበሮቻቸው እድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ ያበረክቱ ዘንድ ትምህርትና ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋሉ፡፡ ለኅብረተሰቡ በተለይም ለወጣቱና ለሴቶች ስለ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ምንነትና ጥቅም ያስተዋውቃሉ፤

6. ማኅበራት በአካባቢ ፣ በክልል ፣ በሀገር አቀፍ ፣ በአህጉር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ በመደራጀትና አባሎቻቸውን በሚገባ በማገልገል የኅብረት ሥራ ማኅበራትን እንቅስቃሴ ያጠናክራሉ፤

2. Cooperative societies are democratic organizations controlled by their members who actively participate in setting their polices and making decisions. Every member has equal voting rights and accordingly one member shall have one vote.

3. Members shall receive devidendes from profit according to their shares and contribution after deducting and setting aside an amount necessary for reserve and social services.

4. Cooperative societies are authonomous self help organizations controlled by their members. If they enter into agreement with other organizations or raise capital from external sources shall do so on terms that ensure democratic control by their members and maintain their autonomy.

5. Cooperative societies provide education and training for their members, elected representatives, managers and employees so as to enable them to contribute effectively to the development of their societies. They inform the general public particularly the youth and women about the nature and benefit of cooperative societies.

6. Cooperative societies serve their members most effectively and strengthen the societies movement by working together through local, national, regional and international structures.

7. ማኀበራት ባፀደቋቸው ፖሊሲዎች አማካኝነት በአካባቢያቸው ለሚገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎች ዘላቂ ልማትን ለማምጣት የሚያስችል ተግባር ያከናውናሉ፡፡

7. Cooperative societies work for the sustainable development of their communities through policies approved by their members.

## ክፍል ሁለት

## ስለ ማኀበራት አመሠራረትና ምዝገባ

## PART TWO

## Formation and Registration of Cooperative Societies

### 6. የመሠረታዊ ኀብረት ሥራ ማኀበራት አመሠራረት፣

1. መሠረታዊ የኀብረት ሥራ ማኀበራት በተወሰነ አካባቢ በሚኖሩ ወይም በሚሰሩ ወይም በተመሳሳይ ሙያ በተሰማሩ ፍቃደኛ ግለሰቦች ይመሠረታሉ፤
2. የመሠረታዊ ኀብረት ሥራ ማኀበራት አባላት ቁጥር ከ 10 ሊያንስ አይችልም፤
3. የዚህ አንቀጽ ፣ ንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የአንድን ማኀበር ኢኮኖሚያዊ ብቃት ሊያስገኝ የሚችለውን የአባላት መነሻ ቁጥር አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያወጣው የአደረጃጀት መመሪያ ይወሰናል፡፡

### 6. Formation of Primary Cooperative Societies

1. A primay cooperative society shall be established by voluntary persons who live or work within a given area or who are engaged similar profession;
2. The number of members in a primary cooperative society to be established shall not be less than ten.
3. Without prejudice the provisions of sub-Article (2) of this Article, the appropriate authority may determine in the directive of organizational structure, the minimum number of members that could make a cooperative society economically feasible.

### 7. የኀብረት ሥራ ማኀበራት ዩኒዬን አመሠራረት

1. ተቀራራቢ ዓላማ ያላቸውና ተመሳሳይ ተግባራትን የሚያከናውኑ መሠረታዊ የኀብረት ሥራ ማኀበራት በጋራ የሚያስተሳስራቸው አንድ ዩኒዬን ሊመሠርቱ ይችላሉ፤

### 7. Formation of Cooperative Society Unions

1. Primary cooperative society having similar objective and performing similar activities may establish a union that tie them in common;

2. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዩኒዩን መሥራች አባል መሠረታዊ ማኅበራት ቁጥር ከሁለት በላይ መሆን ይኖርበታል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ ቢኖርም አግባብ ያለው ባለሥልጣን የአንድን ዩኒዩን ኢኮኖሚያዊ ብቃት ሊያስገኝ የሚችለውን የመሠረታዊ ማኅበራት መነሻ ቁጥር እና የካፒታል መጠን በሚያወጣው መመሪያ ሊወሰን ይችላል፡፡

2. The number of member of founders in cooperative society union shall not be less than two primary cooperative societies.

3. Notwithstanding sub-Article (2) of this Article, the appropriate authority may determine in the directive to be issued the minimum number of members and the amount of capital that could make a union enconomically feasible.

## 8. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ፌዴሬሽን አመሠራረት

## 8. Formation of Cooperative Society Federation

1. ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸው የኅብረት ሥራ ማኅበራት ህብረቶች /ዩኒዬኖች/በክልል ደረጃ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ፌዴሬሽንን ሊመሠርቱ ይችላሉ፤

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከህብረት ሥራ ማኅበራት ፌዴሬሽኑ ጋር ተመሳሳይ ዓላማ ያላቸውና ተመሳሳይ ተግባራትን የሚያከናውኑ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የፌዴሬሽኑ አባል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

1. Unions of cooperative society having similar objective may establish federation of cooperative society, in regional level.

2. Without prejudice to the provisions of sub-Article (1) of this Article, primary cooperative society having similar objective and performing similar activities may be the member of the Federation.

## 9. የኅብረት ሥራ ማኅበራት ዓይነቶች፡-

1. አንድ ማኅበር የምርት ወይም የአገልግሎት ወይም ሁለቱንም ተግባራት የሚያከናውን ሊሆን ይችላል፤

## 9. Types of Cooperative Societies

1. A society may engage in either production or service rendering activities or both.

2. በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ ማንኛውም የኀብረት ሥራ ማኀበር የሚሰራበት የሥራ መስክ በመተዳደሪያ ደንቡ ይወሰናል፤
3. የተለያዩ የኀብረት ሥራ ማኀበራት ዓይነቶች ብሔራዊ ክልሉ በሚኖረው ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ አገልግሎት የሥራ ዘርፎች ውስጥ ሊደራጁ ይችላሉ፡፡

## 10. የማኅበር ስምና አድራሻ፣

1. ማንኛውም ማኀበር የራሱ የሆነ መጠሪያ ስም እና መለያ ምልክት ይኖረዋል፤
2. በማንኛውም ማኀበር ስም መጨረሻ 'ኃላፊነቱ የተወሰነ የኀብረት ሥራ ማኀበር' የሚሉት ቃላት መጻፍ ይኖርባቸዋል፤
3. አንድ ማኀበር በተመዘገበበት ስም ሌላ ተመሳሳይ ማኀበር ሊጠቀምበት አይችልም፡፡ ተመሳሳይ ማኀበራት ግን አንድ ዓይነት ምልክት ሊጠቀሙ ይችላሉ፤
4. አንድ ማኀበር ቋሚና አግባብ ባለው አካል የተመዘገበ አድራሻ ይኖረዋል፡፡

## 11. ስለ ማኀበር ምዝገባ፣

1. ማንኛውም ማኀበር አግባብ ባለው ባለሥልጣን መመዝገብ አለበት፡፡



2. Any society established pursuant to this proclamation, the field of activities to be engaged in shall be determined by the by-laws of the society.
3. Different types of cooperative societies may be organized in the service of economic and social work sector, in the National Region.

## 10. Name and Address of a Society

1. Any society shall have its own name and distinguishing mark.
2. Words "Cooperative society and limited liability" shall appear in the name of every society.
3. a name registered by one society shall be used by any other society. But similar society may use the same distinguishing mark.
4. A society shall have permanent address registered by the appropriate body.

## 11. Registration of a Cooperative Society

1. Any society shall be registered by the appropriate authority.

2. ማንኛውም ማኅበር እንደተቋቋመ የምዝገባ ማመልከቻውን ከሚከተሉት ጋር አያይዞ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ያቀርባል፡፡

ሀ. የመሥራች ስብሰባ ቃለ ጉባኤ፤

ለ.የማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በበቂ ቅጅዎች፤

ሐ. የማኅበሩ አባላት ስም ፣ አድራሻና ፊርማ፤

መ.የማኅበር አባላት ሆነው የሚመዘገቡት ግለሰቦች በዚህ አዋጅና በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ በተወሰነው መሠረት አባል ለመሆን ብቁ መሆናቸውን የሚያስረዱ ሌሎች ዝርዝር መግለጫዎች፤

ሠ. የሚመዘገበው ማኅበር ከመሠረታዊ ማኅበር በላይ ከሆነ የአባል ማኅበራትን ስም አድራሻና የሥራ አመራር ቦርድ አባላት ፊርማ፤

ረ. የማኅበሩ የአጭር ፣ የመካከለኛና ረጅም ጊዜ ዕቅድ፤

ሰ. የማኅበሩን አዋጭነት የሚያሳይ ወቅታዊና ሶሺዮ ኢኮኖሚያዊ ጥናት ፤

ሸ. የመነሻ ካፒታሉ መጠንና የኘው ተሰብስቦ በሕጋዊ የፋይናንስ ተቋም መቀመጡን ፣ ሕጋዊ የፋይናንስ ተቋም በሌለበት ደግሞ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያማክረው ቦታ መቀመጡን የሚያረጋግጥ ሰነድ፤

ቀ. ማኅበሩ የሚሰራበት ቦታ መግለጫ፤

በ. ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎች የሚወሰኑ ሌሎች ጉዳዮች የያዙ መግለጫዎች፡፡



2. Any society, when established, shall submit an application for registration together with the following particulars to the appropriate authority:

a. Minutes of the founders meeting;
b. the by-laws of the society with ample copies;
c. name, address and signature of the members of the society;
d. Other detailed description which proves that the requested members of the society have met the requirements for membership in accordance with the provisions of the this proclamation and the by-laws of the society;
e. name and address of members of the society and signature of members of board of management, if the registered society is above primary society level;
f. short, medium and long term plan of the society;
g. The feasibility study that shows the current socio-economy of the society;
h. Documents showing that the amout of capital of the society and the capital has been collected and eposited in legal finance institution if there is no legal finance institution in the area, that it has been deposited in a place where the appropriate authority has recommended;
i. The description of the land on which the society operates;
j. Other particulars that may be specified in the regulations or directives to be issured for the implementation of this proclamation.

3. አግባብ ያለው ባለሥልጣን የቀረበለትን የምዝገባ ማመልከቻ መርምሮ የተሟላ መሆኑን ሲያረጋግጥ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በአንድ ቀን ተኩል ውስጥ ማኀበሩን መዝግቦ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡ በዚህም የምስክር ወረቀት ላይ ማኀበሩ የተመዘገበበት ቀን ይጠቀሳል፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ እስከ /ሸ/ የተዘረዘሩት መስፈርቶች የተሟሉ መሆናቸውን አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሲያረጋግጥ ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ የሚያገለግል ጊዜያዊ የምስክር ወረቀት ሰጥቶ የተቀሩት መስፈርቶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲሟሉ ማስደረግ ይችላል፡፡ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ቋሚ የምስክር ወረቀት የማይወስድ ኅ/ስራ ማህበር ህጋዊ ሰውነቱን ያጣል፣ ከመዝገብም ይሰረዛል፤

5. አግባብ ያለው ባለሥልጣን አመልካቹን ማኀበር መመዝገብ አይገባውም ሲል የወሰነ እንደሆነ ምክንያቱን በጽሑፍ በማድረግ ለማኀበሩ ወኪሎች ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በ2 ቀናት ውስጥ መግለጽ አለበት፡፡ ይህም ሲሆን የአመልካቹ ማኀበር ወኪሎች በውሳኔው የማይስማሙ ከሆነ የዳኝነት ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ይግባኝ ማለት ይችላሉ፤

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ/3/ መሠረት የተሰጠ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማኀበሩ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የተመዘገበ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ይሆናል፤

3. The appropriate authority shall register a society and issue a certificate of registration within one ans half day, when it is satisfied that the application for registration submitted to it has fulfilled the requirements for registration. The date of registration of the society shall be stated on the certificate.

4. When the appropriate authority checked that the specified criteria from sub-Article 2(a) to (h) of this Article are fulfilled, it shall give temporary certificate that serve not more than a year and cause to fulfill other criterias within the prescribed time. The cooperative society, that shall not take its permanent certificate within a year, shall loose its legal personality and revocated from the registration;

5. When the appropriate authority rejects the application for the registration of a society; It shall give a written explanation to the representatives of the society wihin 2(two) days. The representatives may appeal to the court which has jurisdiction on the decision of the appropriate authority.

6. The certificate of registration issued to a society pursuant to sub-Article (3) of this Article is enough evidence, to prove that a society registered in accordance with this proclamation.

7.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት በህጋዊ መንገድ የተመዘገበ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማኅበር ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ከተቋቋመበት መርህና ዓላማ አንፃር ተጨማሪ የንግድ ፍቃድ ሳያስፈልገው በማንኛውም ሥራ ላይ መሰማራት ይችላል፤

8.ማንኛው ማኅበር ከተቋቋመበት ዓላማ፣ መርህ እና ህግ ውጪ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ በዚህ አዋጅ የተፈቀደለትን ሥራ እንዳይሰራ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ሊታገድ ይችላል፡፡ ማህበሩ ለደረሰበት የፍታብሄር ጉዳት ተጠያቂ አካላትን የስራ አመራር ኮሚቴው ወይም የስራ አመራር ቦርዱ ወይም አግባብ ያለው ባለስልጣን በህግ የመጠየቅ መብት አለው፤

9.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /8/ መሠረት የታገደ ማኅበር ጠቅላላ ጉባዔው ዕግዱ እንዲነሳለት አግባብ ላለው ባለስልጣን ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፤

10.ጥያቄውን የተቀበለው አግባብ ያለው ባለሥልጣን የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እግዱ እንዲነሳለት ያቀረበው ምክንያት በቂና ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው እግዱን ሊያነሳ ይችላል፡፡ ዕግዱን ያላነሳ እንደሆነ ያላነሳበትን ምክንያት ለማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በጽሑፍ ያሳውቃል፤

[

11.አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሰጠው ምክንያት ያልተስማማ ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

## 12.የሥራ ክልል፣

በዚህ አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማኅበር የሥራ ክልል በመተዳደሪያ ደንቡ ይወሰናል፤

7. Any cooperative society registered legally pursuant to sub-Article (3) of this Article, shall engage in any work, inline with its establishment principle and objective, without requiring additional trade license.

8. When any society is found working out of its establishement objective, principle and law, the appropriate authority may suspend, not to do the permitted work by this proclamation. The management committee or the management board or the appropriate authority shall have a right to request with law, the accountable bodies, for the civil damage occurred on the society;

9. The general assembly of a suspended society, pursuant to sub-Article /8/ of this Article, may submit a petition for the removal of the suspension to the appropriate authority.

10. The appropriate authority who received the question of the general assembly of the society about the removal of the suspension, may, remove the suspension, when the submitted reason is enough and appropriate. When it fails to remove the suspension, it informs by writing to the general assembly of the society.

11. When the general assembly disagreed with the reason given by the appropriate authority, may appeal to the court which has jurisdiction.

## 12. Working Region

The working region of any cooperative society established pursuant to this proclamation shall be determined by the by-laws of the society.

## 13.የሕግ ሰውነትና የኃላፊነት ደረጃ

1.ማንኛውም ማህበር በዚህ አዋጅ አንቀጽ /11/ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ የሕግ የሰውነት መብት ይኖረዋል፤

2.የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ አንቀጽ /11/ ንዑስ አንቀጽ /4/ መሠረት ጊዜያዊ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማኀበር ለ 1 ዓመት ህጋዊ የሰውነት መብት ይኖረዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ የቀሩትን አስፈላጊ መስፈርቶች ካሟላ ቋሚ የሆነ የህጋዊ ሰውነት መብት ማረጋገጫ የሚሰጠው ይሆናል፤

3.ማንኛውም ማኅበር ኃላፊነቱ የተወሰነ ስለሆነ ካለው ጠቅላላ ካፒታል በላይ በእዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

## 14.ስለ ማኅበራት መተዳደሪያ ደንብ

1. እያንዳንዱ ማኀበር የራሱ መተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል፤
2. የማንኛውም ማኀበር መተዳደሪያ ደንብ ይዘት የሚከተሉትን ይጨምራል፡-
   - ሀ. የማኅበሩን ስምና አድራሻ፤
   - ለ. የማኀበሩን ራዕይ ፣ ተልዕኮ ፣ ዓላማ ፣ የኀብረት ሥራ እሴቶችና መርሆዎች፤
   - ሐ. የማህበሩን ተግባርና አስተዳደራዊ መዋቅር፤
   - መ. የማህበሩን የሥራ ቦታ አካባቢ፤
   - ሠ. የማህበሩ አባል ለመሆን የሚያበቁ መመዘኛዎችን፤

## 13.Juridical Personality and Level of Responsibility

1. Any society, registered pursuant to sub-Article /3/ of Article /11/ of this proclamation, shall have juridical personality from the date of its registration.

2. Without prejudice to the provisions of sub-article /1/ of this Article, Pursuant to sub-article /4/ of Article /11/ of this Article shall have a judicical personality for one year a society which is given a temporary certificate. Permanaent juridical personality certificate shall be given, if other necessary requirements are fulfilled within this time.

3. Any society shall not be liable beyond its total asset since it has limited liability.

## 14. By-Laws of the society

1. Every society shall have its own by-laws.
2. The contents of the by-laws of any society shall include the following particulars:
   a. Name and address of the society;
   b. Objectives, mission, vision principles and values of cooperative society;
   c. Duties and administrative structure of a society;
   d. Working place (area) of the society;
   e. Requirements necessary for membership of the society;

ረ. ስለ ማኅበሩ አባላት መብትና ግዴታዎች፤

ሰ. አባላት ከማኅበሩ ስለሚወጡበትና ስለሚመለሱበት ሁኔታ፤

ሸ. ስለ ማኅበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ/ቦርድ ሥልጣን፣ ኃላፊነትና ተግባር፣

ቀ. ስለ ማኅበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ አባላትና ሌሎች የሥራ ኃላፊዎች ምርጫ፣ የሥራ ጊዜ እንዲሁም ከኃላፊነት ስለሚወገዱበት ሁኔታ፤

በ. ስለ ስብሰባ ጥሪ፣ አካሔድና ድምፅ አሰጣጥ፤

ተ. ስለ ትርፍ አመዳደብና ክፍፍል፤

ቸ. ስለ ማኅበሩ የገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም፣ የበጀት ዓመት እና የሂሳብ ምርመራ

ኀ. ስለ ብድር አወሳሰን፤

ነ. ስለ ማኅበሩ ሠራተኞች አቀጣጠርና አስተዳደር ፤

ኘ. ይህንን አዋጅ የማይቃረኑ እና አግባብነት ያላቸው ሌሎች ጉዳዮች፡፡

3. የአንድ ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ሊሻሻል ይችላል፡፡ ሆኖም ማንኛውም የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ሊፀና የሚችለው አግባብ ላለው ባለሥልጣን ቀርቦ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፤

4. የማንኛውም ማኅበር መተዳደሪያ ደንብ እንዲሻሻል ሲወሰን የተደረገው ማሻሻያና በዚህ አዋጅ መሠረት የተላለፈ የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ በበቂ ቅጅዎች ተዘጋጅቶ ውሳኔው በተላለፈ በአስር /10/ ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው ባለሥልጣን መቅረብ አለበት፤

f. The rights and duties of members of the society;

g. Conditions for return and withdrawal from membership;

h. The powers, duties and responsibilitites of management committee or board;

i. Conditions for election, term of office as well as dismissal of management committee or board and other management bodies of the society;

j. Conditions for calling of meeting, procedures and voting of the society;

k. Allocation and distribution of profit;

l. Having and usage of finance, budget year and auditing of the society;

m. Determinations of loans;

n. Administration and recruitment of employees;

o. Other appropriate particulars not contray to this proclamation.

3. By-laws of a society may be amended by the special resolution of the general assembly. However, the amendement of the by-laws of the society shall be effective on the date of its submission to and registration by the appropriate authority.

4. Where the society decides on the amendement of its by-laws enough copies of the amendement and the special resolution of the society made in accordance with this proclamation shall be submitted to the appropriate authority within ten /10/ days from the date of the decision.

5. አግባብ ያለው ባለሥልጣን የተደረገው የመተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ ይህንን አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም የወጣ ደንብን ወይም የአደረጃጀት መመሪያን የማይቃረን መሆኑን ሲያረጋግጥ ማሻሻያውን መዝግቦ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በ /1/ ቀን ውስጥ ለማኅበሩ ማስረጃ ይሰጠዋል፡፡

5. The appropriate authority shall register the amendment and give evidence or its registration within one/1/ day, starting from the application is submitted to the society, where it is satisfied that the amendement of the by-law is not contrary to this proclamation and regulations or an organization directives issued for the implementation of this proclamation.

## 15. ስለ ማኅበራት ውህደትና መከፋፈል

1. አንድ ማኅበር በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ ራሱን በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ማህበራት ሊከፋፈል ወይም፤
2. ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ ማህበራት ጋር በመዋሃድ አዲስ ማህበር ሊመሠረት ይችላል፤
3. የማህበር መዋሃድ ወይም መከፋፈል ልዩ ውሳኔ ተፈጻሚ የሚሆነው የነዚህ ማህበራት አባላትና እዳ ጠያቂዎች የተከፈላቸው ወይም የክፍያ ዋስትና የተሰጣቸው መሆኑ ተረጋግጦ ልዩ ውሳኔው አግባብ ባለው ባለስልጣን ሲመዘገብ ይሆናል፤
4. በውህደት የተፈጠረው ማህበር ሲመዘገብ ወይም አንድ የነበረ ማኅበር የተከፋፈለ እንደሆነ የተፈጠሩትን ማኅበራት ሲመዘገቡ የቀድሞው ማኅበር ወይም ማኅበራት ምዝገባ ይሰረዛል ፣ ነባር ኃላፊነቱ/ ኃላፊነታቸውም ይቀራል፤

## 15. Amalgamation and Divisions of Societies

1. The general assembly of a society through a special resolution may form a new society by dividing itself into two or more societies; or
2. By amalgamating itself with one or more societies, it may establish a new society.
3. The special resolution on the amalgamation or division of the society shall be effective on the date of its registration by the appropriate authority upon verifying that the members and creditors of the society have been paid off or their payment is guaranteed.
4. The previous registration of societies shall be canceled from the register as soon as newly formed society by amalgamation or by division are registered; the former responsibility/ responsibilities are canceled.

5. በውህደትና በመከፋፈል ህልውናቸውን ያጡ ማኅበራት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ መሠረት በተመዘገበው የማህበሩ ልዩ ውሳኔ ላይ በተመለከተው ዝርዝር መሠረት አዲስ ወደተቋቋመው /ወደተቋቋሙት ማህበር/ ማህበራት ይተላለፋሉ፡፡

## ክፍል ሦስት

## የማህበር አባላት ፣ መብቶችና ግዴታዎች

### 16. የማህበር አባል ለመሆን የሚያበቁ ሁኔታዎች

የሚከተሉትን የሚያሟሉ ማንኛውም ሰው የማህበር አባል መሆን ይችላል፡-

1. መሠረታዊ ማህበር ከሆነ እድሜው 14 ዓመት የሞላው፤
2. የማህበሩን የመመዝገቢያ ክፍያና ቢያንስ ዝቅተኛውን የዕጣ ብዛት መግዛት የሚችል፣
3. የማህበሩን ዓላማዎችና መተዳደሪያ ደንብ የተቀበለና ግዴታዎቹን ለመፈጸም ፍቃደኛ የሆነ፤
4. ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጡት ደንቦችና መመሪያዎች የሚወሰኑ ሌሎች ሁኔታዎችን የሚያሟሉ፤
5. ከመሠረታዊ ማህበር በላይ ከሆነ ደግሞ አግባብ ባለው ባለሥልጣን የተመዘገበ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፡፡

5. The rights and duties of a societies which have lost their identities by amalgamation and division shall be transferred to the newly established society/ societies as particulars indicated in the registered special resolution of society pursuant to sub-Article /3/ of this Article.

## PART THREE

## The Rights and Duties of Members of a Society

### 16.Requirements Necessary for Membership of a Society

Any individual may become a member of a society where:

1. He has attained the age of 14 if it is a primary society;
2. He is able to pay the share capital and the registration fee required by the society;
3. He is willing to implement his obligation and observe the objectives and by-laws of the society;
4. he fulfills other requirements which may be specified in the regulation and directives to be issued for the implementation of this proclamation;
5. It is registered with the appropriate authority if it is a society above the primary society.

## 17. የአባላት መብትና ግዴታ፣

1. ማንኛውም የማህበር አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-
   ሀ. ማህበሩ የሚሰጠውን ማናቸውንም አገልግሎትና ጥቅም የማግኘት፤
   ለ. በማህበሩ ጉባኤዎች ላይ የመካፈልና ድምጽ የመስጠት፤
   ሐ. በየደረጃው የማህበሩ አመራር ቦታዎች የመምረጥና የመመረጥ፤
   መ. ጥቅሞቹ ተከብረውለት በጥያቄው መሠረት ከማህበሩ የመሰናበት፡፡
2. ማንኛውም የማህበር አባል የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፣
   ሀ. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ መመሪያዎችና ውሳኔዎች የማክበር፤
   ለ. በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያ መሠረት የሚሰጡትን ሥራዎች የማከናወን፤
   ሐ. የማህበሩን የጋራ ንብረት የመንከባከብ፤
   መ. ተሳትፎን መሠረት ባደረገ መንገድ ተጨማሪ ዕጣ የመግዛት ወይም ዕጣን የማስወጣት፤
   ሠ. ማህበሩ ችግር ሲያጋጥመው ከጐኑ የመቆምና ችግሩ እንዲወገድ አስፈላጊውን ጥረትና ድጋፍ የማድረግ፡፡

## 18. ከአባልነት ስለመሰናበትና ወደ ማህበሩ ስለመመለስ፣

1. ማንኛውም አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከማህበሩ ሊሰናበት ይችላል፡-
   ሀ. በራሱ ጥያቄና ፍቃድ፤

## 17. Rights and Duties of Members

1. Any members of a society shall have the following rights:
   a. To obtain any services and benefits according to his participation in the society;
   b. To participate in the meetings of the society and to vote;
   c. To elect and be elected in every level of managerial position of a society;
   d. To withdraw form the society on his request with payment of benefits.
2. Any member of a society shall have the following duties:
   a. To respect the by-laws, directives and decisions of the society;
   b. To perform those activities which ought to be performed in accordance with the by-laws and directives of the society.
   c. To protect the common property of the society;
   d. To buy additional share or cause same based on the participation;
   e. To give the necessary strive and support and to stand along on the side whin the society faces problem.

## 18. Dismissal and Return to Membership

1. Any membe of a society may leave the society on the following reasons:
   a. On his question and initiave;

ለ. ማህበሩ የጣለበትን ግዴታዎች ባለማክበሩ፤

ሐ. በማህበሩ ላይ ጥፋት በመፈፀሙ ምክንያት ጠቅላላ ጉባኤው ሲወስን፡፡

2. ከማህበሩ የተሰናበተ ማንኛውም የማህበሩ አባል የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መብቱ ይጠበቅለታል፤

3. በራሱ ጥያቄና ፍላጐት መሠረት የተሰናበተ ማናቸውም አባል በሥራ አመራር ኮሚቴ/ቦርድ ውሳኔ ተመልሶ አባል ለመሆን ይችላል፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ (ለ) እና (ሐ) መሠረት የተሰናበተ አባል ተመልሶ አባል ለመሆን የሚችለው በጠቅላላ ጉባኤው ሲፈቀድለት ብቻ ይሆናል፡፡

## 19. ስለ ዕጣ ክፍያ፤

1. ማንኛውም ማህበር ሥራውን ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልገውን ካፒታል ማግኘት እንዲችል እኩል ዋጋ ያላቸውን ዕጣዎች በጠቅላላ ጉባኤ አስወስኖ እንዲሸጡ ያደርጋል፤

2. ማንኛውም ማህበር ሲመሠረት በጠቅላላ ጉባኤ እንዲሸጥ ከተወሰነው የዕጣ መጠን ውስጥ ቢያንስ 1/5ኛው ወይም 20% ማህበሩ እንደተመሠረተ መሸጥ አለበት፡፡ ቀሪውን ዕጣ ደግሞ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት አራት ዓመታት ውስጥ መሸጥ ይኖርበታል፤

3. በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሠረት እንዲሸጥ የተወሰነው የዕጣ መጠን ተሸጦ ሲጠናቀቅ ተጨማሪ ካፒታል ካስፈለገ ተጨማሪ ዕጣዎች እንዲሸጡ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እንደገና ሊወስን ይችላል፤

b. On his violation of the duties vested to it;

c. When it is decided by the general assembly because of committing faults;

2. The rights of any dismissed member shall be respected in accordance with the by-laws of the society.

3. Any member, who is dismissed from the society by his question and initiative, may become a member of the society by the decision of management committee or board.

4. Any dismissed person, pursuant to sub-article 1(b) and (c) of this Article, may become a member of the society only if he obtains the approval of the general assembly.

## 19. Payment of Shares

1. Any society, to obtain the required capital to begin his work, shall sell shares having equal price by the decision of the general assembly.

2. When any society established, at least 1/5 or 20% of the share shall be sold, from the amount of shares to be sold decided by the general assembly at the society established. The reaming shares shall be sold within four years starting from the establishment of the society.

3. When the amount of shares decided to be sold finished pursuant to the decision of the general assembly, the general assembly of the society shall decide again to sell additional shares when additional capital is required.

4. ማህበሩ የሚሸጠው ዕጣ በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የሚከፈል ሊሆን ይችላል ዝርዝሩም በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ይሆናል፤
5. አንድ አባል በጠቅላላ ጉባኤው እንዲሸጥ ከተወሰነው የዕጣ መጠን ውስጥ ከ 10% በላይ ድርሻ ሊኖረው አይችልም፤
6. ማንኛውም ማህበር ለሚሸጠው ዕጣ መጠን የማህበሩን መርህ በማይቃረን ሁኔታ የተወሰነ ዕጣ የማህበሩ አባል ላልሆነ ሰው መሸጥ ይችላል፤
7. የካፒታል እጥረት ያጋጠመው ማህበር የማህበሩን መርህ በማይቃረን ሁኔታ የተወሰነ ዕጣ የማህበሩ አባል ላልሆነ ሰው መሸጥ ይችላል፤
8. ከአባላት ውጪ ላለ ሰው የሚደረገው የዕጣ ሽያጭ ዝርዝር ሁኔታ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፡፡

4. The shares sold by the society may be in cash or in kind. Particulars shall be determined by the by-laws of the society.
5. No member shall hold more than 10% within the amount of share capital decided to be sold by the general assembly.
6. Any Society may sell limited shares to a person, who is not member of the society, for the amount of shares to be sold, without contradicting the principles of the society
7. A society faced constraints of capital, may, without contra- dicting the principles of the society, sell limited shares to a person who is not member of the society.
8. Particular conditions, to sell shares to person who is not a member of a society, shall be determined by the by-laws of the society.

## 20. ስለ አባላት መዝገብና ልዩ ልዩ ሰነዶች

1. ማንኛውም ማህበር ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የገቢና የወጪ ደረሰኞች፣ ሌሎች መሠረታዊ ሰነዶችና ልዩ ልዩ መዛግብት ሊኖሩት ይገባል፤
2. ማንኛውም ማህበር አግባብ ያለው ባለሥልጣን ባዘጋጀው የአደረጃጀት መመሪያና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተገለፁ ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ የአባላት መዝገብ ማደራጀትና መያዝ አለበት፡፡

## 20. Register of Members and Different Documents

1. Any society shall have a receipt of revenue and expenditure, other basic documents and different registers necessary for the work starting form its establishment.
2. Any society shall, organize and keep register of members that hold particular issues specified in the organization directive prepared by the appropriate authority and by-laws of the society.

## 21. ስለ ድምፅ አሰጣጥ፣

1. ማንኛውም አባል በማህበሩ ውስጥ ያለው የዕጣ መጠን ከግምት ውስጥ ሳያስገባ በስብሰባ ላይ ተገኝቶ የሚሰጠው ድምጽ አንድ ብቻ ይሆናል፤
2. ማንኛውም የመሠረታዊ ማህበር አባል በስብሰባ ላይ በአካል ተገኝቶ ድምጽ መስጠት ይኖርበታል፤
3. ከመሠረታዊ ማህበር በላይ ባሉት ደረጃዎች የሚቋቋም ማህበር ድምጽ የሚሰጠው በተወካዮች አማካኝነት ይሆናል፤
4. በማህበሩ መተደደሪያ ደንብ በተለየ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር በመደበኛ ወይም በአስቸኳይ ጉባኤ የሚተላለፍ ውሳኔዎች በአባላት አብላጫ ድምጽ ይወሰናሉ፡፡ ድምፁ እኩል በእኩል የተከፈለ ከሆነ የጉባኤው ሰብሳቢ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡

## 22. ዕጣን ወይም ጥቅምን ስለማስተላለፍ

1. ማንኛውም አባል ዕጣውን ወይም ጥቅሙን ለማስተላለፍ የሚችለው
   ሀ. ዕጣውን ወይም ጥቅሙን ከአንድ ዓመት ላላነሰ ጊዜ ይዞት የቆየ ሲሆን እና፤
   ለ. የማስተላለፍ ተግባር በሥራ አመራር ኮሚቴ/ቦርድ የተፈቀደ ሲሆን ነው፡፡
2. አንድ የመሠረታዊ ማህበር አባል ሲሞት ዕጣው ወይም ጥቅሙ በማህበሩ መዝገብ ውስጥ በወራሽነት ለሰየመው ወይም ሟች ወራሽ ያልሰየመ ከሆነ በሕግ ለመውረስ ለሚችል ወራሹ ይተላለፋል፡፡ ይህም የሚሆነው ወራሹ የማህበሩ አባል ከሆነ ወይም ለመሆን ፍቃደኛነቱን ከገለጸ ነው፤

## 21. Voting

1. Every member shall, regardless of the member of shares he has in the society, only one vote at the meeting of the society;
2. Every members in a primary society shall personally be present at the meeting of the society to cast a vote;
3. Member of a society above primary level shall cast a vote through their representatives;
4. Decisions of the regular or extraordinary meeting shall be passed by a majority vote unless special condition is specified in the by-laws of the society. In cause of tie; however; the chairperson shall have a decisive casting vote.

## 22. Transfer of Share or Benefit

1. No transfer by a member of his share or benefit in a society shall be valid unless;
   a. The member has held such share or benefit for at least one year before he transfers;
   b. The transfer is approved by the management committee or board;
2. On the death of a member of a primary society, his share or benefit shall be transferred to one of his heirs designated as such in the register of society or failing such designation to his legal heir at law, and where such heir is a member or is willing to be a member.

3. ወራሹ የማህበሩ አባል ካልሆነ ወይም አባል ለመሆን የማይፈልግ ወይም አባል እንዲሆን የማይፈቀድለት ከሆነ የሟቹ የዕጣው ዋጋና ጥቅም ይከፈለዋል፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ዕጣ ወይም ጥቅም የሚተላለፍለት አባል ዕጣው በዚህ አዋጅ አንቀጽ /19/ ንዑስ አንቀጽ /5/ መሠረት የተወሰነውን ገደብ የሚያልፍ ሆኖ ሲገኝ ልዩነቱ በገንዘብ ይከፈለዋል፤
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት የተደረገ ማስተላለፍ ወይም ክፍያ ሦስተኛ ወገኖች በማህበሩ ላይ በሚያቀርቡት ጥያቄ ምክንያት አይሻርም፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ አመራር አካላት

### 23. ስለ ማህበሩ የበላይ አካል

የማንኛውም ማህበር የበላይ አካል የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ይሆናል፡፡

### 24. የጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር፣

የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የማህበሩን አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች እየገመገመ ውሳኔዎችን ያሳልፋል፤
2. የማህበሩን ረቂቅ መተዳደሪያ ደንብና ውስጠ ደንብ መርምሮ ያፀድቃል፤
3. የማህበሩን የሥራ አመራር ኮሚቴ/ቦርድ/ ፣ የቁጥጥር ኮሚቴና ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች ይመርጣል፣ ይሽራል፤
4. የማህበሩን የዕጣ መጠንና ዋጋ ይወስናል፤
5. የማህበሩን የተጣራ ትርፍ ድልድል ይወስናል፤

3. Where such heir is not a member and does not wish to become or is not admitted as a member, he shall be paid the value of the share or benefit of the deceased member.
4. If the shares or benefit to be transferred to a member under sub-Article /2/ of this Article are found to be beyond the limitation prescribed in sub-Article /5/ of Article /19/ hereof, the member shall be paid the difference in cash.
5. The transfer or payment concluded in pursuance of sub-Article /2/ of this Article shall not be reversed due to the claims paused by third parties on the society.

## PART FOUR

## Management Bodies

### 23. Supreme Organ of a Society

The supreme organ of any society shall be the general assembly.

### 24. Powers and Duties of the General Assembly

The general assembly of a society shall have the following powers and duties

1. Pass decisions after evaluating the general activities of the societies;
2. Examine and approve the draft by-laws and internal regulations of the society;
3. Elect and dismiss the members of the management committee, board, control committee and other sub-committees;
4. Determine the amount of shares and price of the society;
5. Decide on how the annual net profit of the society is distributed;

6. በሂሳብ ምርመራ ሪፖርት ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤
7. የሥራ ክንውን ሪፖርቶችን ያዳምጣል ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፤
8. በዚህ አዋጅ መሠረት ማህበሩ ከሌላ ማህበር ጋር እንዲዋሃድ ወይም እንዲከፈል ይወስናል፤
9. ዓመታዊ የሥራ ዕቅድንና በጀትን ያፀድቃል፣
10. በሥራ አመራር ኮሚቴ/ቦርድና ሌሎች ኮሚቴዎች የሚቀርቡለትን ማናቸውንም ጉዳዮች ይወስናል፡፡

## 25. ጠቅላላ ጉባኤ ስለመጥራት፣

1. ማንኛውም ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤
2. ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት ከግማሽ በላይ ሲገኙ ምልዐተ ጉባኤ ይሆናል፤
3. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ተጠርቶ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ በድጋሚ ጠቅላላ ጉባኤ ይጠራል፡፡ በሁለተኛ ጊዜ በተጠራው ጠቅላላ ጉባኤ ከጠቅላላ አባላት 1/3ኛዎቹ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ እንደተሟላ ተቆጥሮ በተገኙ አባላት መደበኛ ጉባኤው ይካሄዳል፤
4. ለሁለተኛ ጊዜ በተጠራው ጠቅላላ ስብሰባ የተገኙት አባላት ቁጥር ከጠቅላላ አባላቱ ከ 1/3ኛ በታች ከሆነ ማንኛውም ጉዳይ ለ 3ኛ ጊዜ ጥሪ ተደርጎ የማህበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ/ቦርድ አባላትን ጨምሮ በእለቱ ጥሪውን አክብረው በተገኙት የጉባኤ አባላት አብላጫ ድምጽ ይወሰናል፤

6. Give decision on the audit report;
7. Hear work reports and give proper decision;
8. Decide that a society either be amalgamated with another society or be divided in pursuance of this proclamation;
9. Approve the annual work plan and budget;
10. Decide any issue submitted by the management committee, board and other committees.

## 25. Calling of General Assembly

1. The general assembly of any society shall met at leas once in a year;
2. The presence of more that half of the members of the general assembly, shall constitute a quorum.
3. When the regular meetings of the general assembly fails to constitute the quorum, it shall be called again. Among the total members if one-thirds of the members present at a second meeting, by considering as a quorum the regular meeting shall be held by the members present at a meeting.
4. When the number of members present at the second meeting less that one-thirds from the total members, there is a third meeting and decisions passed by majority vote of members present at the meeting including members of the management committee or board.

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /4/ መሠረት ምልዓተ ጉባኤ ሳይሟላ የተካሄደ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ የሚያሳልፈው ውሳኔ የጉባኤው አባላት በተገኙበት እንደተላለፈ ይቆጠራል፤

6. የማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ/ቦርድ ወይም ከጠቅላላ ጉባኤ አባላት መካከል የአንድ ሦስተኛው ስብሰባ እንዲደረግ ሲጠይቁ የ 15 ቀን ቅድሚያ ማስታወቂያ በማውጣት የጠቅላላ ጉባኤው አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፤

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /6/ መሠረት አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲደረግ የሥራ አመራር ኮሚቴ/ቦርዱ ጥሪ ያላደረገ እንደሆነ አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጥሪውን ያደርጋል፡፡ ይኸውም ጠቅላላ ጉባኤ በሥራ አመራር ኮሚቴ/ቦርድ እንደተጠራ ይቆጠራል፡፡

## 26. ስለ ሥራ አመራር ኮሚቴ/ቦርድ አቋም

1. እያንዳንዱ የመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበር ቁጥራቸውና አመራረጣቸው በመተደደሪያ ደንቡ የሚወሰን አባላትን የያዘና ለጠቅላላ ጉባኤው ተጠሪ የሆነ የሥራ አመራር ኮሚቴ ይኖረዋል፤

2. እያንዳንዱ የከፍተኛ ደረጃ የኅብረት ሥራ ማህበር ቁጥራቸውና አመራረጣቸው በመተዳደሪያ ደንቡ የሚወሰን አባላትን የያዘና ለጠቅላላ ጉባኤው ተጠሪ የሆነ የሥራ አመራር ቦርድ ይኖረዋል፤

3. የየትኛውም ዓይነት ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ/ቦርድ አባላት የሥራ ዘመን ሶስት ዓመት ይሆናል፤

5. When the general assembly fails to constitute a quourum pursuant to sub-Article /4/ of this Article, in such case be deemed to have been considered decisions passed by the presence of members.

6. If the managemenet committee or board ro one-thirds of the members of the general assembly require a meeting to be called, an extera ordinary meeting may be held giving 15 days prior notice.

7. Where the management committee or board fails to call an extra ordinary general assembly in accordance with sub-Article /6/ of this Article such meeting shall be called by the appropriate authority and shall in such case bedeemmed to have been called by the management committee.

## 26. The Status of Management Committee or Board

1. Every primary cooperative society shall have a management committee which is Accountable to the general assembly and whose members and manner of election to be determined in the by-laws of the society.

2. Every higher level cooperative society shall have a managemenet board which is accountable to the general assembly and whose numbers and manner of election to be determined in the by-laws of the society.

3. The term of office of the management committee or board of any kind of society shall be there years.

4. የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ አባላት ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጡ አይችሉም፡፡ በተመረጡበት የሥራ ዘመን ውስጥ ጥፋት ከፈፀሙ ደግሞ በማናቸውም ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤው ውሣኔ ሊሻሩ ይችላሉ፤

5. የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ አባላት በማናቸውም ሁኔታ ሥራቸውን ሲለቁ በሥራ ዘመናቸው ያከናወኑትን ተግባር የማስመርመርና በስማቸው ወጪ ያደረጉትን ማናቸውንም ንብረት የመመለስ ግዴታ አለባቸው፤

6. አመራር አካላቱ ሆን ብለው ወይም በቸልተኝነት ባጠፉት ጥፋት በስራ ላይ እያሉም ሆነ ከኃላፊነት ከተነሱም በኋላ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

## 27. የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ ሥልጣንና ተግባር፤

የሥራ አመራር ኮሚቴ/ቦርድ ሥልጣንና ተግባር በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ይጨምራል፡፡

1. የማህበሩን ዓላማዎች ለማሳካት የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን የመተዳደሪያ ደንብና ልዩ ልዩ መመሪያዎችን ይቀርጻል ፣ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያስወስናል ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

2. ሥራ አስኪያጅና ሌሎች ቅጥር ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ከችሎታቸውና ከሥራ ኃላፊነታቸው ጋር የተጣጣመ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ይወስናል፤

4. Members of the management committee shall not be elected for more that two consecutive terms. They may be dismissed at any time by the general assembly if they committed fault within their term of office.

5. When the members of the mamagement committee leave their office for whatever reasons, they have the obligation to causes to be inspected the activities they performed during their term of office and to return any property taken by their names.

6. The Leaders shall be accountable with appropriate law, where they are in effect or after outgoing by faults they do deliberately or in carelessness;

## 27. Powers and Duties of the Management Committee or Board

The powers and duties of the management committee or board shall be determined in pursuance of the by-laws and in particular shall include the following:

1. Design policies, by laws and different directives that enables the society to implement its objectives; and upon approval of the general assembly implement same.

2. Recruit the manager and other staff; determine their salary and benefits that coincide with their abilities and responsibilities.

3. ለሥራ አስኪያጁ ተግባርና ኃላፊነቱን ወስኖ ይሰጣል ፣ በዚሁ መሠረት መፈፀሙን በቅርብ ይከታተላል ፣ ይቆጣጠራል፤
4. ጠቅላላ ጉባኤው ያሳለፋቸውን ፖሊሲዎችና ውሳኔዎች ተግባራዊ ያደርጋል ፣ ይከታተላል፤
5. የማህበሩ ካፒታል የሚጎለብትበትን መንገድ ያፈላልጋል፤
6. የስብሰባ ቃለ ጉባኤዎች በአግባቡ ይይዛል፤
7. የማህበሩን መዛግብትና ሂሳብ በሚገባ ይቆጣጠራል፤
8. በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት ማህበሩን ወክሎ ውል ይዋዋላል ፣ ይበደራል፤
9. የግዥ የሽያጭና የብድር ፖሊሲ ረቂቆችን አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል ፣ ሲፀድቁለትም በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፤
10. የአባላትን ወይም የአባል ማህበራትን ችግር መሠረት ያደረገ የአጭር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፣ ለጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ይገመግማል፣
11. የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፤
12. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ጠቅላላ ጉባኤውን ይጠራል፤
13. በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

3. Determine and give duties and responsibilities of the manager; in accordance with this, follow up and supervise the implementation of same;
4. Implement, follow up policies and decisions passed by general assembly;
5. Facilitate conditions to promote the capital of the society;
6. Maintain properly the minutes of a meeting;
7. Control documents and books of accounts of the society;
8. Enter into contracts, borrow in the name of the society pursuant to the power vested to it by the by-laws of the society;
9. Prepare and submit procurement, sale and loan draft policy to the general assembly; upon approval cause the implementation of same.
10. Prepare short, medium and long-term work plan and budget which is prepared based on the problem of members of the societies; cause to be approved by submitting it to the general assembly; and evaluate the implementation of same;
11. Submit performance report to the general assembly
12. Call general assembly in accordance with the by-laws of the society;
13. Perform such other duties entrusted to him by the general assembly;

## 28. የቁጥጥር ኮሚቴ አቋም

1. እያንዳንዱ ማህበር ቁጥራቸው በመተዳደሪያ ደንቡ የሚወሰን አባላትን የያዘና ለጠቅላላ ጉባኤ ተጠሪ የሆነ የቁጥጥር ኮሚቴ ይኖረዋል፤
2. በማንኛውም ዓይነት ማህበር የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን ሶስት ዓመት ይሆናል፤
3. የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ከሁለት ተከታታይ የሥራ ዘመን በላይ ሊመረጡ አይችሉም፡፡ ሆኖም በተመረጡበት የሥራ ዘመን ውስጥ ጥፋት ከፈፀሙ በማናቸውም ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤው ሊሻሩ ይችላሉ፤
4. አመራር አካላቱ ሆን ብለው ወይም በቸልተኝነት ባጠፉት ጥፋት በስራ ላይ እያሉም ሆነ ከኃላፊነት ከተነሱም በኋላ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

## 29. የቁጥጥር ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር፣

የቁጥጥር ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰን ሆኖ በተለይ የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

1. የሥራ አመራር ኮሚቴው /ቦርዱ ኃላፊነቱን በትክክል መወጣቱን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
2. የማህበሩ ገንዘብና ንብረት በትክክል በሥራ ላይ መዋሉን ይቆጣጠራል፤
3. የማህበሩ ልዩ ልዩ እንቅስቃሴዎች በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ፣ ውስጠ ደንብና መመሪያዎች መሠረት መከናወናቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
4. በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 28. Status of Control Committee

1. Every society shall have a control committee which is accountable to the general assembly and the number of which shall be specified by the by-laws of the society.
2. The term of office of members of any kind of society shall be three years.
3. No members of the control committee shal be elected for more than two consecutive terms. They may, while in term of office, be dismissed any time by the general assembly if they committed fault.
4. 4.The leaders shall be accountable with appropriate law, where they are in effect or after outgoing by faults they do deliberately or in carelessness;

## 29. Powers and Duties of the Control Committee

The powers and duties of the control committee shall be determined in pursuance of the by-laws and inparticular shall include the following:

1. Follow up that the management committee or board is carrying out its responsibilities properly;
2. Follow up that the funds and property of the society is properly untilized;
3. Follow up, and suprervise that the various activities of the society are carried out, pursuant to they by-laws, internal regulations and directives of the society;
4. Performs such othe duties entrusted to it by the general assembly.

### 30. ስለ ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች፣

በማናቸውም ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች እንደየማህበራቱ ዓይነትና የሥራ ባህርይ ተቋቁመው በመተዳደሪያ ደንቡ በሚወሰነው መሠረት ተግባርና ኃላፊነታቸውን ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡

## ክፍል አምስት

## የማህበር ልዩ መብቶች

### 31. ለማህበር ዕዳ ክፍያ ቅድሚያ ስለመስጠት፣

በማናቸውም ሕግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገ ቢኖርም ማንኛውም ማህበር ከአንድ አባል ወይም ኅ/ስራ ማህበር ወይም ከማንኛውም አካል ላይ የሚፈለገው የዕዳ ክፍያ ከመንግሥት እዳ በስተቀር ከሌሎች ዕዳዎች ክፍያ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡

### 32. የአባላትን ዕጣ ወይም ጥቅም ስለማቻቻል፣

የማንኛውም አባል ዕጣ ወይም ጥቅም ማህበሩ ለሚፈልግበት የዕዳ ክፍያ ማቻቻያ ሊደረግ ይችላል፡፡

### 33. ዕጣን ወይም ጥቅምን ለማስከበር ወይም ለመሸጥ ስላለመቻሉ፣

በዚህ አዋጅ አንቀጽ /32/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አባል በማህበሩ ውስጥ የሚኖረው ዕጣ ወይም ጥቅም አባሉ ከሌላ ወገን ላለበት ዕዳ ማስከፈያ ሲባል ሊከበር ወይም ሊሸጥ አይችልም፡፡

### 34. ስለ ይርጋ

የይርጋ ጊዜን አስመልክቶ በወንጀል እና በፍታብሔር ህግ ወይም በሌሎች አግባብ ባላቸው ህጎች የወጡ የይርጋ ዘመን አቆጣጠሮች ለዚህ አዋጅም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

### 30. Other Sub-Committees

Other sub-committees established as the kind of the society and nature of work may carry out their duties dand responsibilities that to be determined by the by-law.

## PART FIVE

## Special Privileges of the Society

### 31. Priority of Claims by Society

Notwithstanding any provision to the contrary in any law, debts owed to the society by member or cooperative society or from any entity, shall take precedence over all other debts, except the debt owed to the Government.

### 32. Set-off in Respect of Share or Benefit of Members

The shares or benefits of any member may be set-off for debts due to the society such a member.

### 33. Share or Benefit not Liable to Attachment or Sale

Without prejudice the provisions of Article /32/ of this proclamation the share of benefit of a member in any society shall not be liable to other party to attachment or sale.

### 34. Period of Limitation

Pursuant to Period of Limitation, the numberings of period of limitation, that have been issued by the criminal and the civil law or by other appropriate laws, shall be applicable for this proclamation.

## 35. የመንግሥት ድጋፍ፤

1.በኢንቨስትመንትና በሌሎች ሕጐች የተፈቀዱት ማበረታቻዎች ለኀብረት ሥራ ማኀበራት መፈቀዳቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የህብረት ሥራ ማህበራት የሚከተሉትን ድጋፎችና ማበረታቻዎች በተለየ ሁኔታ ያገኛሉ፡፡

ሀ. በዚህ አዋጅ መሠረት የሚደራጅ ማንኛውም ማህበር የሚያገኘው ገቢ ከገቢ ግብር ነፃ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግለሰብ አባላት ከሚያገኙት የዕጣ ድርሻ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የገቢ ግብር ይከፍላሉ፤

ለ. ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ሆኖ ማንኛውም ማህበር ተግባራቱን ለማከናወን የሚያስፈልገው መሬት በከተማ ክልል የሆነ እንደሆነ በምደባ እና በገጠር አካባቢዎች የሆነ እንደሆነ ደግሞ በነጻ ይሰጠዋል፡፡

2. የኀብረት ሥራ እንቅስቃሴን የማጐልበት ፣ የሰው ኃይልን የማሰልጠንና ጥናትና ምርምር የማካሄድ ኃላፊነት የተሰጠው ተቋም በመመሥረትና በማደራጀት ረገድ የሙያ ድጋፍ ያደርጋል፤

3. የሕብረት ሥራ ማህበራትን በፋይናንስ አቅርቦት የሚደግፍ ልዩ ፈንድ ሊቋቋም ይችላል፤

4. ማንኛውም ማህበር ከማህበሩ ጋር በተያያዘ ጉዳይ ፍ/ቤት ላለበት ክርክር ከሚከፈል የዳኝነት ክፍያ ነፃ ነው፤



## 35. Government Assistance

1. Without prejudice to incentives permitted under investment laws and other laws, societies which are organized and registered under this proclamation shall be gained the following support and incentives in special condition:

   a. Income of a society, established as per this proclamation shall be exempted from income tax. However, individual members shall pay income tax on their dividends based on the appropriate law.

   b.The particulars shall be determined by a regulation to be issued for the implementation of this proclamation any society that needs land to perform its activities, shall be given with allocation where it is in urban and shall be freely given a land where it is in rural areas.

2. Give professional support by establishing and organizaing an institution responsible for promoting cooperative movement, rendering man-power training and conducting studies and research.

3. May establish special fund that support cooperative societies in finance supply.

4. Any society shall be free from court fee in a dispute held in court in connection with affairs of the society.

5. የኅ/ስራ ማህበራት አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም በክልሉ ፍትህ ቢሮና በበታች አካላቱ አማካኝነት ነጻ የህግ ድጋፍ አገልግሎት ያገኛሉ፡፡

## ክፍል ስድስት

## የማህበራት ንብረትና ገንዘብ

### 36. የማህበር ንብረትና ገንዘብ የማይከፋፈል ስለመሆኑ፣

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ /37/ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ለአባላት እንዲከፈል ከሚወሰነው በስተቀር በእንቅስቃሴው ላይ ያለ የአንድ ማህበር ንብረትና ገንዘብ ለአባላቱ ወይም ለሌላ ወገን አይከፋፈልም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው እንደተጠበቀው ሆኖ ማህበሩ የሚፈርስ ከሆነ ‘ለማህበራዊ አገልግሎት ተብሎ’ የተቀመጠው ገንዘብ በአካባቢው ላለ ሌላ ማህበር ፣ ወይም በክልሉ ለተቋቋመ ልዩ የኀብረት ሥራ ፈንድ እንዲገባ ሆኖ ቀሪውን ማህበሩ ሲፈርስ ያሉ አባላት ሊከፋፈሉ ይችላሉ፤
3. በስጦታ ወይም በውርስ የተገኘ ንብረት ማህበሩ እስካለ ድረስ በወል ንብረትነት ያገለግላል፡፡ ሆኖም ማህበሩ የሚፈርስ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ለኀብረት ሥራ ፈንድ ገቢ ይሆናል ወይም ለሌላ ተመሳሳይ ማህበር ይሰጣል፡፡

### 37. የተጣራ ትርፍ አደላደል

1. አንድ ማህበር ከሚያገኘው የተጣራ ትርፍ ላይ 30 በመቶው እየተቀነሰ ለኪሳራ መጠባበቂያ ይሆን ዘንድ ለዚሁ ዓላማ በሚከፈተው የቁጠባ ሂሳብ ይቀመጣል ፡፡ ለመጠባበቂያ ሂሳቡ የሚቀመጠው ገንዘብ ከማህበሩ ካፒታል 30 በመቶ እስኪሞላ ድረስ ነው፤

5. The cooperative societies shall get free service of legal support by appropriate authority or with regard to regional Justice Bureau and by lower bodies.

## PART SIX

## Asset and Funds of the Society

### 36. Indivisibility of Asset and Funds of the Society

1. Except as otherwise prescribed under sub-Article /2/ of Article /37/ of this proclamation, asset and fund of a society that are in movement, shall not be divided for the members or any other party.
2. Without prejudice to sub-article /1/ of this Article, if the society dissolved, funds that are deposited as “Social Service” will be entered into the nearby other society or special cooperative fund to be established in the region and the remainder may be divided to those who are members when the society dissolved.
3. The property obtained from donation or successions shall serve the common property until the society exists. However, when the society dissolved, pursuant to sub-Article /1/ of this Article shall be given to the cooperative fund or to other similar society.

### 37. Allocation of Net Profit

1. A society shall deduct 30% of the net profit obtained with the view to allocating for deficit reserve and shall be put in saving account opened for this objective. The money has to be deposited in reserve until it become 30% of the capital of the society.

2. ከመጠባበቂያ የሚቀረው የተጣራ ትርፍ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ይከፋፈላል፣
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አባላት ካልሆኑ ግለሰቦችና ድርጅቶች ጋር በመናገድና የአባላት ገንዘብ ባልሆነ ካፒታል ተሳትፎ የተገኘ ትርፍ ለአባላት ክፍፍል አይውልም፣
4. አባላት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት ከሚያገኙት የተጣራ ትርፍ ተጨማሪ ዕጣ ሊገዙበት ይችላሉ፡፡

## 38. ስለ መበደር ወሰን

አንድ ማህበር ከአባላቱ ወይም ከሌሎች ድርጅቶች የሚበደረው ብድር መጠንና ሁኔታ በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ይሆናል፡፡

## 39. ስለ ማበደር ወሰን

1. ማናቸውም ማህበር ለአባላቱ ወይም በዚህ አዋጅ መሠረት ለተቋቋመ ሌላ ማህበር ካልሆነ በስተቀር ብድር መስጠት አይችልም፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ /1/ ድንጋጌ መሰረት ማህበሩ የሚያበድርበት ወለድ መጠን በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፡፡

# ክፍል ሰባት

# ስለ ሂሳብ ቁጥጥርና ምርመራ

## 40. ስለ ሂሳብ ምርመራ

1. አግባብ ያለው ባለሥልጣን በየዓመቱ የማንኛውንም ማህበር ሂሳብ በራሱ ወይም እርሱ በሚወክለው ሰው አማካኝነት እንዲመረመር ያደርጋል፣

2. The net profit remained from reserve shall be divided pursuant to the decision of the by-laws of the society.
3. Without prejudice to the provisions of sub-Article /2/ of this Article , profit obtained from trade together with individual, organizations and capital invested by people who are not members shall not be divided to members.
4. Members may buy additional share by the net profit obtained pursuant to sub-Article/ 2/ of this Article.

## 38. Restrictions on Borrowings

A society shall receive loans from its members or other organizations to such extent and on such conditions as may be specified in the by-laws of the society.

## 39. Restrictions on Loans

1. Any society shall not extend loans other than to its members or a society established with this proclamation.
2. Pursuant to the provisionof sub-article /1/ of this Article, the society amount of interest to give a credit shall be determined by the by-laws of the Society.

# PART SEVEN

# Audit and Inspection of an Account

## 40. Audit of an Account

1. The appropriate authority shall audit or causes to be audited the accounts of any society every year by himself or by person assigned by it.

2. አግባብ ያለው ባለሥልጣን ወይም እርሱ የሚወክለው ሰው ለሂሳብ ምርመራ አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን የሂሣብ መዛግብትና ሰነዶች ፣ ቃለ ጉባኤዎች የቃልና የጽሁፍ ማስረጃዎች ፣ የማህበሩን አሰራርና መርሆዎች ማንኛውንም ጥሬ ገንዘብ ያልተከፈለ እዳን የዋስትና ሰነዶችንና የሃብቱን ዋጋና ኃላፊነትን ጨምሮ ይመረምራል፤

3. አግባብ ያለው ባለስልጣን የሂሳብ ምርመራ ሪፖርቱን ምርመራው ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ሰባት የስራ ቀናት ውስጥ ለተመርማሪው ማህበር ማድረስ አለበት፤

4. ተመርማሪው ማህበር የሂሳብ ምርመራ ሪፖርቱ እንደደረሰው የጠቅላላ ጉባኤውን የመሰብሰቢያ ወቅት ጠብቆ በማቅረብ ያስፀድቃል፡፡ ሆኖም አስቸኳይ የኦዲት ግኝት ካጋጠመ መደበኛ የመሰብሰቢያ ጊዜውን ሳይጠብቅ ጠቅላላ ጉባኤው በአስቸኳይ እንዲጠራ በማድረግ የሂሳብ/ምርመራ ሪፖርቱን ማስፀደቅ ይኖርበታል፤

5. ጠቅላላ ጉባዔው በኦዲት ሪፖርቱ ላይ ችግር አለበት ብሎ ካመነ ሂሣቡ እንደገና እንዲመረመር አግባብ ላለው ባለሥልጣን ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ አግባብ ያለው ባለሥልጣንም የቀረበለትን ጥያቄ መርምሮ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጣል፤

2. The appropriate authority or the person assigned by him examines books of accounts and documents, minutes, oral and written evidences, procedures and principles of the society, cash, overdue debts, securities, assets necessary for auditing including liabilities.

3. The appropriate authority shall submit the audit report to the audited society starting from the time of completion within seven working days of the audit.

4. The audited society on receiving the audit report cause the approval of same by the general assembly by keeping the time of meeting. Where as, the urgent crisis findings is encountered,not awaiting the regular time of meeting , cause the general assembly to be called urgently, cause the approval of same;

5. When the general assembly belives that there is a problem on the audit report, may submit a question to the appropriate authority to be audited again. The appropriate authority give the necessary decision by examing the question submitted to it.

6. ተመርማሪ ማኀበሩ በተላከለት የኦዲት ሪፖርት ውስጥ እንዲወሰዱ በቀረቡ የማስተካከያ ሃሣቦችና አስተያየቶች መሠረት ከ45 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ተገቢውን እርምጃ ወስዶ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ያሳውቃል፤

7. ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀፅ /4/ ስር እንደተደነገገው የኦዲት ሪፖርቱ ለጠቅላላ ጉባኤው ቀርቦ አለመጽደቅ በማህበሩ ላይ የደረሰውን ጉዳት የሚመለከታቸውን ሁሉ በሀላፊነት ከመጠየቅ አያድናቸውም፡፡

6. The audited society, pursuant to corrective recommendations and opinions that shall be taken on the audit report sent to it, shall inform to the appropriate authority, by taking appropriate measures not more than 45 days.

7. As the provision stipulated herein above, under sub-article /4/, the audit report not to be submitted and approved by the general assembly, the damage that occurred on the society that shall not protect all pertinent bodies of same from responsibility.

## 41. ስለ ቁጥጥር እና ድንገተኛ የሂሳብ ምርመራ

1. አግባብ ያለው ባለሥልጣን በአንድ ማህበር አሠራር ላይ ችግር ደርሷል ብሎ ሲያምን ወይም ጥቆማ ሲደርሰው ድንገተኛ ቁጥጥርና የሂሳብ ምርመራ ያደርጋል፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያለው ባለሥልጣን
   - ሀ. ከሥራ አመራር ኮሚቴው ወይም ከቦርዱ አባላት መካከል 2/3ኛው ሲጠይቁ፡፡
   - ለ. ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት ውስጥ ከአንድ ሶስተኛ ያላነሱት በጽሁፍ ሲጠይቁ የሂሳብ ምርመራ ያደርጋል፤
3. አግባብ ያለው ባለሥልጣን አንድ ማህበር በተቋቋመበት እና በተመዘገበበት አኳኋን እየሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ በፈለገ ጊዜ የቁጥጥርና ኢንስፔክሽን ሥራ ያከናውናል፤

## 41. Inspection and Sudden Audit

1. The appropriate authority shall take sudden inspection and audit when it believed that there is a problem or when it received information;
2. Without prejudice to the provisions of sub-Article /1/ of this Article, the appropriate authority:
   - a. When it is requested by two-third of management committee or board members.
   - b. audit when it is requested by members not less than one-third of the general assembly members of the society in writing.
3. The appropriate authority does controlling and inspecting works, to ensure that whether a society works pursuant to its establishement and register objectives or not.

4. የሂሳብ ምርመራ ወይም ቁጥጥር ውጤትን ለማወቅ የፈለገ የማህበሩ አባል ውጤቱን በፈለገበት ጊዜ የማወቅ መብት አለው፡፡

## 42. የመርማሪ አካላት ሥልጣንና ተጠያቂነት

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ /40/ እና /41/ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የማህበራትን ሂሳብ እንዲመረምር አግባብ ባለው ባለሥልጣን የታዘዘ የሂሳብ መርማሪ የሚከተሉትን ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-
   ሀ. የአንድን ማህበር አቋም ፣ የሥራ አፈፃፀም መዛግብትና የገንዘብ ሁኔታ የመመርመር፤
   ለ. ለምርመራው አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን ማናቸውንም ማስረጃዎች እንዲቀርቡለት የማዘዝ፤
   ሐ. በሂሳብ ምርመራ ወቅት ማስረጃ ለማቅረብ ፈቃደኛ ያልሆኑትን ወይም የተጭበረበረ ማስረጃ ለማቅረብ የሞከሩትን ወይም የሂሳብ ምርመራው በሰላማዊ መንገድ እንዳይፈፀም ለማደናቀፍ የሚሞክሩትን ለማህበሩ በማሳወቅ አግባብ ባለው ሕጋዊ አካል እርምጃ እንዲወሰድባቸው የማስደረግ፤
   መ. የገንዘብ መሰብሰቢያ ሰነድ ወይም የገቢ ደረሰኝ ጠፋብን በሚሉ ተመርማሪዎች ላይ ከሂሳብ መርማሪዎች ውጭ ባሉ በሚመለከታቸዉ አግባብ ያለዉ ባለስልጣን ባለሙያዎች ሌሎች ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን መነሻ በማድረግና ጉዳዩን ለጠቅላላ ጉባኤው በማቅረብ ምን ያህል የገንዘብ መጠን ሊሰበሰብበት ይችል እንደነበር ከተወሰነ በኋላ ሂሳቡን የመመርመር፣

4. Member of a society has the right to know the audit or result of the control any time he wants to know.

## 42. Powers and Accountability of the Auditor

1. Without prejudice to the provisions of Article /40/ and /41/ of this proclamation, the auditor assigned by the appropriate authority to audit a society's account, shall have the following powers and duties:
   a. to audit the status, work performance documents and financial condition of a society;
   b. to order to be submitted any necessary evidences for auditing;
   c. Cause measure to be taken by the appropriate legal body by informing to the society, on those who fail to submit evidence or who attempt to submit deceptive evidence or who attempt to interrupt, the audit not to be accomplished peacefully.
   d. Audit the account after determined the amounts of money that had been collected, cause to start other different evidences and submitting the issue to the general assembly, on the lost cash receipt voucher by professionals pertinent to the appropriate authority, with the exception of account auditors.

2. የአንድን ማህበር ሂሳብ እንዲመረምር ወይም ቁጥጥር እንዲያደርግ አግባብ ባለው ባለሥልጣን የታዘዘ ማንኛውም የሂሳብ መርማሪ ከዚህ በታች የተመለከቱትን ጥፋቶች የፈፀመ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል፡-

ሀ. በሂሳብ ምርመራ ጊዜ ሆነ ብሎ ተመርማሪውን ያለ አግባብ ባለ እዳ ካደረገ ወይም የተመርማሪዉ ያልሆነውን ሂሳብ በተመርማሪው ላይ ከጨመረ፤

ለ. ተመርማሪውን ሆነ ብሎ በእዳ እንዳይጠየቅ ካደረገ ወይም፣ የገንዘብ ጉድለት የታየበትን ማንኛውንም የማህበር አመራር አካል፣ አባል ወይም ቅጥር ሠራተኛ ጉድለት ዕዳ ያላግባብ በመቀነስ በማህበሩ ላይ ጉዳት እንዲደርስ ያደረገ፡፡

2. Any auditor, who is assigned by the appropriate authority, to audit or to control the accounts of a society, shall be accountable where commits faults that are stated herein under:

a. When, in the course of audit he intentionally makes the audited improperly liable; or include account not to be the audited;

b. Intentionally, causes the audited not to be liable of his debt improperly, or who cause damage on the society by reducing the debt of any leader, member or employee who robs finance of the society inappropriately

## 43.የተመርማሪዎች ግዴታ

1. አግባብ ያለው ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ አንቀጽ /40/ እና /41/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የአንድን ማህበር ገንዘብ ፣ ሰነድና ንብረት የሚያንቀሳቅሱ አካላት ሂሳብ እንዲያስመረምሩ ሲጠየቁ ሂሳቡን የማስመርመር ግዴታ አለባቸው፤
2. አግባብ ያለው ባለሥልጣን ወይም እርሱ የወከላቸው ሰዎች ለሂሳብ ምርመራ አስፈላጊ የመሰላቸውን ማስረጃዎች ሁሉ እንዲቀርቡላቸው ሲጠይቁ ተመርማሪው የተሟላ ማስረጃ ወዲያውኑ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

## 43. Duty of the Audited

1. The bodies that run the finance, document and property of the society shall be duty bound to be audited when they are requested to audit their account by the appropriate body by the power vested to it pursuant to Article /40/ and /41/ of this proclamation.
2. When the appropriate authority or the persons assigned by it requested the audited to submit all the necessary evidences for auditing, shall be duty bound to submit full evidences immediately.

## 44. ግዴታዎቹን ባልተወጣ ተመርማሪ ላይ ስለሚከተል የወንጀል ኃላፊነት

1. ማንኛውም የማህበር ተመርማሪ፡-

ሀ. አግባብ ያለው ባለሥልጣን ወይም እርሱ የሚወክለው ሰው ለምርመራ እንዲቀርቡለት የሚጠይቃቸውን የሂሳብ መዛግብትና ሰነዶች ቃለ ጉባኤዎችና ሌሎች ልዩ ልዩ ጽሑፎች እንዲሁም የቃል ማስረጃዎች ያላቀረበ፤

ለ. ሃሰተኛ መሆኑን እያወቀ ወይም እውነተኛ ለመሆኑ በቂ ማስረጃ የሌለውን መረጃ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ወይም እሱ ለወከለው መርማሪ ያቀረበ፤

ሐ. መርማሪው ተግባሩን በሚገባ እንዳያከናውን ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል ሙከራ ያደረገ፣ ወይም በመርማሪው ላይ የዛተ እንደሆነ ድርጊቱ በማስረጃ ሲረጋገጥ ከሶስት አመት በማያንስና ከአስር ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እና ከ30,000.00 ብር በማያንስና ከ100,000.00 ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. ማንኛውም ተመርማሪ የማህበሩን የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ በቸልተኝነት የጣለ ወይም ያጠፋ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ከአንድ አመት በማያንስና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና ከ10,000.00 ብር በማያንስና ከ50,000.00 ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

## 44. Criminal Responsibility on the Audited Person Not Discharging His Duties

1.Any audited society:

a.Fails to make available books of accounts and documents, minutes and other different writing as well as oral evidences which the appropriate authority or the persons assigned by it requires for auditing;

b. Submit to the appropriate authority or to the auditor assigned by it evidence that he knows to be forged or which he has no evidence to be true.

c. One who obstacle the auditor not to do his duties properly or one who attempt to obstacle or one who threat the auditor, when this action is proved by evidence; he shall be punished with rigorous imprisonment not less than three years, and not more than ten years ; and not less than 30,000 ( thirty thousand ) Birr and not more than 100,000 ( hundred thousand ) Birr.

2. Where it is proved by evidence , that any audited person lost or lie down the receipt of revenue of the society 's carlessly, he shall be punished with rigorous imprisonment not less than one years and not more than five years ; and not less than 10,000 ( ten thousand ) Birr and not more than 50,000 ( fifty thousand ) Birr.

3. ተመርማሪው በእምነት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዕቃ ወይም ጥሬ ገንዘብ ለመመለስ ወይም ለመክፈል ወይም የጣለውን ወይም ያጠፋውን የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ማስረከብ ወይም ይኸው የሚገኝበትን ሁኔታ ለማሳየት ወይም ለተገቢው አገልግሎት ያዋለው መሆኑን ለማስረዳት ካልቻለ ንብረቱን ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያልተገባ ጥቅም እንዳዋለው ይገመታል፡፡

3. The audited person rendered material or cash by loyalty or entrusted, to return back or pay or; deliver the lost or lay down receipt of revenue, or he could not cause to realizing, not to show its condition or has been served for the appropriate service; it shall be assumed that the property is conducted for him or another person.

## 45. በሂሳብ ምርመራ ውጤት ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ

1. ተመርማሪው ግለሰብ በምርመራ ውጤቱ ላይ ተመሥርቶ ቅሬታ ካለው የኦዲት ሪፖርቱን ግለሰቡ እንዲያዉቀዉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ በ2 ወራት ጊዜ ውስጥ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ቅሬታውን ያቀርባል፡፡ አግባብ ያለው ባለስልጣንም ጉዳዩን ሲያምንበት በሌሎች መርማሪዎች እንዲታይ ማድረግ ይችላል፡
2. ተመርማሪው ባቀረበው ቅሬታ አማካይነት ጥፋቱ የመርማሪው ሆኖ ከተገኘ በዚህ አዋጅ አንቀጽ /42/ ንዑስ አንቀጽ /2/ ሐ መሠረት መርማሪው ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ጥፋቱ የተመርማሪው ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ሂሳቡ እንደገና ሲመረመር የወጡ ወጪዎችን ተመርማሪው እንዲሸፍን ይደረጋል፡፡

## 45. Complain Submission on the Result of the Audit

1. When the audited individual has complain on the result of the audit, shall submit his complain to the appropriate authority starting from the time he is informed the audit report, within two months. Where the appropriate authority believed on the issue, may cause to be audited by others.
2. Where the fault is the auditor, the auditor shall be accountable pursuant to sub-Article 2(c) of Article /42/ of this proclamation. If the fault is found to be the audited person, where investigation is done again, the audited individual shall cover expenditures that held for the second time.

## 46. በማህበሩ ንብረትና ገንዘብ ላይ ጉድለት ሲደርስ ስለሚኖር የወንጀል ሀላፊነት

1. የሂሣብ ምርመራ ወይም ቁጥጥር በሚደረግበት ጊዜ የማህበሩን ሥራ እንዲያካሂድ ኃላፊነት የተጣለበት ወይም ተጥሎበት የነበረ ማንኛውም የማህበር ተመራጭ ወይም ቅጥር ሠራተኛ፡-
   ሀ. በዚህ አዋጅ፣ አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦች ወይም መመሪያዎችን በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ያልተፈቀደ ክፍያ ፈጽሞ የተገኘ ወይም ለመፈፀም የተዋዋለ፤
   ለ. እምነት በማጉደል ወይም ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት በማህበሩ ንብረት ላይ ጉድለት አድርሶ ከተገኘ፤
   ሐ. የማህበሩ የሆነውን ንብረት ወይም ገንዘብ አላግባብ መውሰዱ ከተረጋገጠ ተቆጣጣሪው ወይም መርማሪው ስለ ሁኔታው እንደ ጉዳዩ አግባብነት ለሥራ አመራር ኮሚቴው፣ ለቦርዱ፣ ለጠቅላላ ጉባኤው ወይም አግባብ ላለው ባለሥልጣን ሪፖርት ያደርጋል፤
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር የተመለከቱትን ጥፋቶች ስለመፈፀሙ የተረጋገጠበት ማንኛውም ሰው ድርጊቱ በኢፌደሪ የወንጀል ህግ የበለጠ የሚያስቀጣ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ከአምስት ዓመት በማያንስና ከአስራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት እና ከ50,000.00 ብር በማያንስና ከ150,000.00 ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣

## 46.The Crime Responsibility for Losses of Property and Finance of the Society

1. Any elected member of the Society or an employee that is or was entrusted with responsibility by the management of the society, where account is audited or inspected.
   a. Had made or contract agreement any payment contrary to the society by-laws of this proclamation, the regulations tobe issued for the execution this proclamation or directives;
   b. Had caused any damages to the assets of the society by breach of trust or willfully or negligently;
   c. Has misappropriated to the property or finance of the society, the inspector or the auditor shall make a report to the management committee, board , the general assembly or, the appropriate authority on the conditions as the case may be.
2. Any person, who is assured that he committed faults stated under sub-article /1/ of this Article, unless his fault is found to be sentenced more with the federal criminal law, shall be punished by imprisonment not less than five years and not more than fifeteen years and not less than 50,000 (fifty thousand) Birr and not more than 150,000 (one hundred fifty thousand) Birr;

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ ፊደል ተራ ቁጥር /ሐ/ ድንጋጌ መሠረት ሪፖርት የቀረበለት አግባብ ያለው ባለሥልጣን ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው በማህበሩ ላይ ያደረሰውን ጉድለት እንዲተካና ስለዚሁ ማስረጃ እንዲያቀርብ እድል ሊሠጠው ይችላል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን እንደሁኔታው ማህበሩ፣ አግባብ ያለው ባለስልጣን ወይም የክልሉ ዐቃቢ ህግ በእምነት አጉዳይ ላይ የፍታብሔር ክስ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት በመመሥረትና በመከራከር እዳውን ከተገቢው ኪሣራ ጋር ያስመልሣል፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዐቃቢ ህግ በፍታብሄር ጉዳይ ማህበራቱን ወክሎ መከራከር የሚችለው ከ150,000 ብር በላይ ለሆነ የገንዘብ ወይም የንብረት ጉድለት ነው፡፡

## ክፍል ስምንት

## ስለ ማኅበራት መፍረስና ሂሳባቸውን ስለማጣራት

### 47. ስለ ማህበር መፍረስ፣

1. አንድ ማህበር በሚከተሉት ምክንያቶች ይፈርሳል፡
   ሀ. እንዲፈርስ የአባላት ልዩ ውሳኔ ሲሰጥ፤
   ለ. የዚህ አዋጅ አንቀጽ /6/ ንዑስ አንቀጽ /3/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ መሠረታዊ ማህበር ከሆነ ለመፍረስ የሚያስፈልገው ዝቅተኛ የአባላት ቁጥር ከ 10 በታች ሲሆን፤

3. Pursuant to the provision stipulated under /c/ of sub-article /1/ of this Article, the appropriate authority who is submitted a report, may give a chance to the pertinent person for issue to replace the loss that he dia on the society and to submit evidence for same; unless otherwise, as deemed as necessary, the society , the appropriate authority or the prosecuter, of the region,shall cause to return back his debt with the appropriate loss, by raising a civil charge on whom un-entrusted, by sue and dialogue with court vested with power;

4. Without prejudice to the provision stated in sub-article/3/ of this Article,t he prosecutor can dialogue with civil cases, by representing the society, for finance or property that shall cost more than 150,000 (one hundred fifty) loss of Birr;

## PART EIGHT

## Dissolution and Winding up of Societies

### 47. Dissolution of a Society

1. A society shall be dissolved on the following reasons:
   a. Where a special resolution for its dissolution is given by the members; or
   b. Without prejudice to sub-Article /3/ of Article /6/ of this proclamation, where the number of members of a primary society falls below ten;

ሐ. ፍርድ ቤት እንዲፈርስ ሲወስን፤

መ. በማህበሩ የሂሳብ ምርመራ ውጤት መሠረት የከሰረና የኪሣራውም መጠን የማህበሩን ህልውና የሚያሳጣ መሆኑን አግባብ ያለው ባለሥልጣን ሲያረጋግጥና በጠቅላላ ጉባኤ ሲወሰን፤

ሠ. ኅ/ስራ ማህበሩ ይህንን አዋጅ፣ አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ መመሪያዎችና መተዳደሪያ ደንብ ተግባራዊ አለማድረጉን ወይም እነዚህን ህጎች የሚጻረር ተግባር መፈፀሙን አግባብ ያለው ባለስልጣን ሲያረጋግጥና የህግ ጥሰቱን ለማስተካከል ፈቃደኛ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀርና አግባብ ያለው ባለስልጣን ኅ/ስራ ማህበሩ እንዲፈርስ ሲወስን፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ማህበር እንዲፈርስ ሲወሰን ማህበሩ አግባብ ላለው ባለሥልጣን የመፍረስ ውሳኔውን በሰባት ቀናት ውስጥ ማሳወቅ ይኖርበታል፤

3. በዚህ አንቀጽ /1/ እና /2/ ሥር ከተደነገገው ውጭ በህገ ወጥ መንገድ ለሚፈርስ ማህበር ፣ ማህበሩ ሲፈርስ የነበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ አባላት ሙሉ ኃላፊነቱን ይወስዳሉ፡፡ በህግም ይጠየቃሉ፡፡

c. When the court decided to be dissolved;

d. When the appropriate authority approved and determined by the general assembly that the society is bankrupt and the amount of deficit cease to exist the society based on the result of the audit;

e. Where the appropriate authority shall ensure, that the society does not implement this proclamation, directives to be issued for the implementation of this proclamation, or execute activities contrary to these laws, and where he is not voluntary to correct the breach of law and , where the appropriate authority shall decide the society shall be dissoluted

2. Without prejudice to the provision of sub-Article /1/ of this Article, a society shall inform the decision of dissolution to the appropriate authority within seven days from the decision for its dissolution.

3. When a society dissolved illegally out of the stipulation of under sub-article /1/ and /2 /of this Article, that had been management committee or board members, during the dissolution of society, shall take full responsibility and asked by law.

## 48. ስለ ሂሳብ አጣሪ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ /47/ መሠረት አንድ ማህበር እንዲፈርስ ሲወሰን አግባብ ያለው ባለሥልጣን የሂሳብ አጣሪ/አጣሪዎች/ ሊመደብ ይችላል፡፡

1. ሂሳብ አጣሪው እንደተመደበ የማህበሩን መዛግብት ፣ ሰነዶችና ንብረት ይረከባል በማህበሩ መብቶች ፣ መዛግብትና ሰነዶች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፤
2. የሂሳብ አጣሪው የማጣራቱን ሥራ እንዳጠናቀቀ ሪፖርቱን አዘጋጅቶ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ያቀርባል፡፡ የማኀበሩን ማዛግብትና ሰነዶች አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያዝዘው ቦታ ያስቀምጣል፡፡

## 49. የሂሳብ አጣሪው ሥልጣንና ተግባር

1. የሂሳብ አጣሪው የሂሳብ ማጣራቱን ሥርዓት ከፍጻሜ ለማድረስ አስፈላጊው ሥልጣን ሁሉ ይኖረዋል፡፡ ሥራውን በሚገባ ለመፈፀም በተለይ የሚከተሉትን ያከናውናል፡፡
   ሀ. ከማህበሩ የሚጠየቀውን ዕዳ መርምሮ የአከፋፈሉን ቅደም ተከተል ይወስናል፤
   ለ. የማህበሩን ሃብትና ንብረት ይሰበስባል፤
   ሐ. ማህበሩን በሚመለከቱ ክርክሮች ተወካይ ይሆናል፤
   መ. ለሂሳብ ማጣራቱ ሥራ መቃናት አስፈላጊ ሲሆን አባላትን ወይም የሥራ አመራር ኮሚቴ /ቦርዱን ለስብሰባ ይጠራል/፤

## 48. Liquidator

Where the dissolution of a society has been decided upon, pursuant to Article /47/ of this proclamation, the appropriate authority may, assign a liquidator/Liquidators.

1. The liquidator shall receive records, documents and properties of the society as soon as he is assigned, he shall also take the necessary measures to protect the rights, records and documents of the society from damages.
2. Upon completion of the winding up proceedings the liquidator shall prepare and submit a repote to the appropriate authority, he shall deposit the records and documents of the society in such places as the appropriate authority may direct

## 49. Powers and Duties of the Liquidator

1. The liquidator shall have all the necessary powers to complete the winding up proceedings. He shall in particular perform the following in order to carry out his duties properly:
   a. investigate all claims against the society and decide on priority of payment among them;
   b. Collect the assets of the society;
   c. represent the society in legal proceedings;
   d. call meetings of the members of management committee or board, as may be necessary for the proper conduct of the liquidation.

ሠ. ማህበሩ የሚፈርስ ስለመሆኑ በታወቀ ጋዜጣ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በተከታታይ ቀናት እስከ ሁለት ወር ተቃዋሚ ካልቀረበ የጠቅላላ ጉባኤ ባፀደቀው እቅድ መሠረት ሀብትና ንብረቱን ለአባላት ያከፋፍላል፡፡

2. የሂሣብ አጣሪው የማጣራቱን ሥርዓት እንደፈፀመ ሪፖርቱን አዘጋጅቶ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ያቀርባል ፤ የማህበሩን መዛግብትና ሰነዶችም አግባብ ያለው ባለሥልጣን በሚያዝዘው ሥፍራ ያስቀምጣል፡፡

## 50. ገንዘብ ጠያቂዎችን ስለመጥራት፤

1. የገንዘብ ጠያቂዎችን ዕዳ አከፋፈል የሂሳብ አጣሪው ሥራ በሚጀምርበት ጊዜ ባዘጋጀው የሃብትና ዕዳ መግለጫ መሠረት ይፈጽማል፤
2. ለገንዘብ ጠያቂዎቹ የማህበሩ መፍረስ ተነግሯቸው አቤቱታቸውን እንዲያስታውቁና ለሚጠይቁትም ገንዘብ ደጋፊ ሰነዶቻቸውን እንዲያቀርቡ ማስገንዘቢያ ይደርሳቸዋል፤
3. በማህበሩ መዝገብ ውስጥ ስማቸው ለተጻፈ ወይም በሌላ አኳኋን ለታወቁ ገንዘብ ጠያቂዎች ስለ ማህበሩ መፍረስ በሪኮማንዴ ደብዳቤዎች በቀጥታ ይላክላቸዋል፡፡ ለሌሎች ግን በጋዜጣ የሚወጡት ማስታወቂያዎች ለሁለት ጊዜ በተከታታይነት በወር አንድ ጊዜ መውጣት አለባቸው፡፡

e. issue the notice in nown news paper about the dissoulution of the society; it shall proced with distribution of asset and property based on theplan approved by the general assembly where no clam is presented within to months from the date of such notice.

2. Upon completion of the winding up proceedings the liquidator shall prepare and submit a report to the appropriate authority, he shall deposit the records and documents of the society in such places as the appropriate authority may direct.

## 50. Calling on Creditors

1. Creditors shall be paid on the basis of a property and liability description prepared by the liquidator upon the commencement of his assisnment.
2. Creditors shall be informed of the dissolution of the society and required to file their claims with supporting documents.
3. The name of creditors written in the society’s records or who are otherwise known shall be notified directly by registered letter. Notice to other creditors shall be given by notice, published intwo successive monthly issues of a newspaper;

## 51.የገንዘብ ጠያቂዎችን መብት ስለመጠበቅ፣

1. ከማህበሩ ገንዘብ ጠያቂዎች የሆኑት ካልተከፈላቸው ወይም የእነርሱን ገንዘብ ለመክፈል በቂ የሆነ ገንዘብ ተቀማጭ ካልተደረገ በቀር ሂሳብ አጣሪዎች የማህበሩን ንብረት በከፊልም ቢሆን ለአባላት ማከፋፈል አይችሉም፤
2. የታወቁት ገንዘብ ጠያቂዎች ማስረጃቸውን ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ የሚከፈላቸው ገንዘብ ልክ በፍ/ቤት ውሳኔ ይቀመጣል፤
3. ገንዘብ ጠያቂዎች ለሚፈልጉት ሂሳብ ተመጣጣኝ የሆኑ ዋስትናዎች ካልተሰጧቸው ወይም የማህበሩ ንብረት አከፋፈል እነዚሁ ግዴታዎች እስኪከፈሉ ድረስ የጊዜ ገደብ ካልተቀመጠለት በቀር ላልተፈፀመው ግዴታ ወይም በክርክር ላይ ላሉት የማህበሩ ግዴታዎች ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ተይዞ መቀመጥ አለበት፤
4. የማህበሩ እዳ ተከፍሎ ካለቀ ወይም ዕዳውን ለመክፈል በቂ የሆነ ገንዘብ መቀመጡ ከተረጋገጠ በኋላ አጣሪዎች ቀሪውን የማህበሩን ሂሳብ ለማህበሩ አባላት በሚገባቸው መጠን ያከፋፍላሉ፡፡ ሆኖም ግን ለማህበራዊ አገልግሎት፣ ስጦታና ውርስ የተቀመጠው ገንዘብ በክልሉ ለሚቋቋመው የኅ/ስራ ፈንድ ወይም በአካባቢው ላለ ሌላ ተመሳሳይ ኅ/ስራ ማህበር ገቢ ይሆናል፡፡

## 51. Protection of the Right of Creditors

1. Until the creditors of the society have been paid or amounts required for payment be deposited, the liquidators may not distribute any part of assets among the members.
2. Where known creditors have failed to present their supporting documents, the amounts owing to them shall be deposited according to the decision of the court.
3. Sums shall be set aside to meet the claims in respect of undertakings of the society which are nto completed or which are under liquidation unless th creditors are guaranteed or distribution of assets is postponed until such undertakings are completed.
4. After the payment of claims have been completed or verified that sufficient deposit for payment has been made, the liquidators may distribute the assets of the society among the members based on the amount due to them. However, the finance, deposited for social service, gift and heirs, shall be revenued for cooperative fund, that shall established in the region or other similar cooperative society found in the local place.

## 52. ማህበርን ከመዝገብ ስለመሠረዝ

1. ሂሣብ ማጣራቱ ሥራ እንደተፈፀመ ማህበሩ የተመዘገበበት የምስክር ወረቀት አግባብ ላለው ባለሥልጣን ይመለሳል፡፡ አግባብ ያለው ባለሥልጣንም ማህበሩን ከመዝገብ ይሰርዛል፡፡ የሚመለከታቸው አካላትም እንዲያውቁት ያደርጋል፤
2. ማህበሩ ከመዝገብ ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ ህልውናውን ያጣል፡፡

## ክፍል ዘጠኝ

## ስለ ክርክሮች አወሳሰን

## 53. ጉዳዮችን በእርቅ ስለመጨረስ

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ /56/ የተመለከቱት ክርክሮች ለሽምግልና ዳኝነት ከመቅረባቸው በፊት ተከራካሪ ወገኖች በሚመርጡት ሶስተኛ ወገን በእርቅ መታየት ይችላሉ፤
2. እያንዳንዱ ወገን አንድ አስታራቂ ይመርጣል የአስታራቂዎች ሰብሳቢ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት ይሰየማል፤
3. የአስታራቂዎችን ሰብሳቢ ለመምረጥ ሁለቱ ወገኖች ስምምነት ላይ ካልደረሱ ሰብሳቢው አግባብ ባለው ባለሥልጣን ይመረጣል፡፡

## 54. ስለ ሽምግልና ዳኝነት፣

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ /56/ የተመለከቱት የህብረት ሥራ ማህበራት ክርክሮች በእርቅ ያላለቁ እንደሆነ ለሽምግልና ዳኝነት ይቀርባሉ፤

## 52. Cancellation of a Society from the Register

1. When the winding up proceedings are completed the certificate of registration shall be returned to the appropriate authority who shall cancel the registration of the society; shall notify it for the pertinent bodies;
2. The society shall, upon the date of such cancellation, cease to exist.

## PART NINE

## Settlement of Disputes

## 53. Conciliation

1. The disputes provided under Article /56/ of this proclamation shall be heard by a third party appointed by the disputing parties before they are referred to the arbitrators.
2. Each party shall choose one conciliator, the chairperson of the conciliator shall be elected on the agreements of both parties.
3. When the two parties fail to reach an agreement on the selection of the chairperson, the chairperson shall be elected by the appropriate authority.

## 54. Arbitration

1. When the disputes provided under Article /56/ regarding cooperative societies are not settled by conciliation they shall be referred to arbitration.

2. ለሽምግልና ዳኝነት ተግባር የሚመረጡ ሰዎች ቁጥራቸው ሶስት ሆኖ የማያዳሉና መልካም ስም ያላቸው መሆን ይኖርባቸዋል፤
3. የሽምግልና ዳኞቹ ክርክሮችን የሚሰሙትና ማናቸውንም ተግባር ሁሉ የሚፈጽሙት አግባብ ባላቸው የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፡፡

## 55. የሽምግልና ዳኞች አመራረጥ፤

1. እያንዳንዱ ወገን አንድ የሽምግልና ዳኛ ይመርጣል፤ ለሽምግልና ዳኝነት ሰብሳቢ እንዲሆን የሚመረጠው ሶስተኛ ዳኛ በጋራ በሁለቱ ወገኖች ይመረጣል፤
2. ሰብሳቢ ዳኛውን ለመምረጥ ሁለቱ ወገኖች ስምምነት ላይ ያልደረሱ እንደሆነ ሰብሳቢ የሚሆነው ዳኛ አግባብ ያለው ባለሥልጣን መርጦ ይሰይማል፡፡

## 56. ለሽምግልና ዳኝነት ስለሚቀርቡ ክርክሮች

1. እምነትን በማጉደል ወይም ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት በማህበሩ ንብረት ላይ ጉድለት አድርሰው የተገኙ አመራር አካላት ወይም ቅጥር ሠራተኞች ወይም አባላት ወይም በዕዳ የሚጠየቁ ሰዎችን ወይም ድርጅቶችን ወይም ኃላፊነት ባለመወጣት ለሚደርስ ጉዳትንና የወንጀል ድርጊቶችን አይመለከቱም፡፡



2. The arbitration shall consist of three persons of high reputation and impartiality.
3. The arbitrator’s shall conduct their hearing and fulfill any of their duties, in accordance with the civil procedure code.

## 55. Appointment of the Arbitrators

1. Each party to the dispute shall appoint one arbitrator the third arbitratory, who shall be the presiding arbitrator, shall be appointed by both parties.
2. The appropriate authority shall appoint the presiding judge when the parties fail to reach an agreement.

## 56. Disputes to be Referred to Arbitration

1. The Leaders who are found cause to fault on the society property, not entrusted or deliberately or with carelessness disputes, or employees or members or persons,who are requested with debt, organizations or the fault occurred or criminal acts done shall not concern in case not discharging the responsibility;

2. የሽምግልና ዳኞች የአንድን ማህበር አቋም፣ የሥራውን አካሄድ፣ ወይም የሥራውን አፈፃፀም አስመልክቶ በዕርቅ ያላለቁትንና ከዚህ በታች የተመለከቱትን ጉዳዮች የማየት ሥልጣን ይኖራቸዋል፡-

ሀ. በአባላት ወይም በቀድሞ አባላትና ወይም በቀድሞ አባላት ወኪሎች ወይም በሞት በተለዩ አባላት መብት ስም ክርክር በሚያቀርቡ ሰዎች መካከል የሚነሳ ክርክር፤

ለ. በአባላቱ በቀድሞ አባላት ወይም በአባላት ወይም በቀድሞ አባላት ወኪሎች ወይም በሞት በተለዩ አባላት ወራሾችና በማህበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ ፣ በማናቸውም አካል በወኪሉ ወይም በማህበሩ ቅጥር ሠራተኛ መካከል የሚነሳ ክርክር፤

ሐ. በማህበሩ ወይም በሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ ወይም በማንኛውም የቀድሞ የሥራ አመራር ኮሚቴ ማንኛውም ተመራጭ ወኪል ወይም ሠራተኛ ወይም የቀድሞ ተመራጭ የቀድሞ ወኪል ወይም የቀድሞ ሠራተኛ ተጠሪ ወራሹ ወይም ወኪሎቹ ወይም በሞት በተለዩ የማህበሩ ተመራጭ ወኪሎች ወይም ሠራተኞች መካከል የሚነሳ ክርክር፤

መ. በአንድ ማህበርና በማናቸውም ሌላ በዚህ አዋጅ በተቋቋመ ማህበር መካከል የሚነሳ ክርክር ፡፡

2.The arbitrators shall have the power to hear disputes not settled by conciliation regarding the organization, management, or operations a society on the following issues:

a. Members or former members or representatives of former members or persons claiming in the name of deceased members; or

b. Members, former members or representatives of members or former members or heirs of deceased members and management committee or board, andy body, his representative or employee of the society;

c. The society or the management committee or board or any former management committee or any electorate, agent or employee or former electorate, former agent or representative of former employee or heirs or representatives or represenetatives of deceased former electorate ro employees

d. Raising disputes between by a society and any other society that is established, with this proclamation.

## 57. የሽምግልና ዳኞች የፍትሐብሔር ሥልጣን

የሽምግልና ዳኞች በዚህ አዋጅ አንቀጽ /56/ መሠረት የሚታዩ ጉዳዮችን በተመለከተ ምስክሮችን ለመጥራት ማስረጃዎችን ለማስቀረብ ትዕዛዝም ሆነ ብይን ለመስጠትና ሌላም ማንኛውንም ህጋዊ እርምጃ ለመውሰድ የፍትሐብሔር ችሎት ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

## 58. አፈፃፀም

በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጥ ማንኛውም ውሳኔ ትዕዛዝ ወይም ብይን በፍትሐብሔር ችሎት እንደተሰጠው ተቆጥሮ አስፈላጊ ሲሆን ፍርድ ቤቶች ውሳኔው፣ ትዕዛዙ ወይም ብይኑ እንዲፈፀም የማስገደድ ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡

## 59. ስለ ፍርድ ቤት ሥልጣን፣

በዚህ አዋጅ አንቀጽ /54/ መሠረት በሽምግልና ዳኝነት በተሰጡ ውሰኔዎች ላይ ለዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይቻላል፡፡

## ክፍል አሥር

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 60. ስለ ማህበር አድራሻ

ማንኛውም ማህበር በዚህ አዋጅ አንቀጽ /10/ መሠረት የተመዘገበ አድራሻ ይኖረዋል፡፡ ማህበሩ አድራሻውን ሲለውጥ በሠላሣ ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት፡፡

## 57. Civil Jurisdiction of Arbitrators

The Arbitrators shall have the same power with regard to the cases provided under Article /56/ of this proclamation, as a civil chilot for the summoning of witness, production of evidence, the issuing of orders or the taking of any legal measures.

## 58. Execution

Any decision, order or award made under this proclamation shall be taken as though made by a civil court, and , where appropriate, the courts shall have jurisdiction to order the enforcement of any such decision, order or award.

## 59. Jurisdiction of Courts

Appeals on the decisions given by the Arbitrators under Article /54/ of this proclamation shall be submitted to High court of the zone.

## PART TEN

## Miscellaneous Provisions

## 60. Address of a Society

Any society shall have an address registered pursuant to Article /10/ of this proclamation. The society shall inform to the appropriate authority of within thirty days, where it changes its address.

**61. መረጃ ስለመስጠት፣**

አንድ ማህበር ስለሚያከናውናቸው ተግባራት አግባብ ላለው ባለሥልጣን መረጃዎችን የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

**62. ይህንን አዋጅ ፣ ደንቦችንና መተዳደሪያ ደንቦችን ለዕይታ ክፍት ስለማድርግ፣**

ማንኛውም ማህበር ይህንን አዋጅ ደንቦቹንና የመተዳደሪያ ደንቦቹን ቅጅዎች በማህበሩ አድራሻ እንዲገኙና በነፃ እንዲታዩ መፍቀድ አለበት፡፡

**63. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ውስጥ ለሰፈሩት ድንጋጌዎች ሙሉ ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**64. ስለተሻሩና ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጐች**

1. የህብረት ስራ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 134/1998 ዓ.ም በዚህ አዋጅ ተሺሯል፡፡
2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ፣ ደንብ መመሪያ የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**65. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች፣**

1. በኀብረት ሥራ ማኀበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 138/1970 እና 85/1986 መሠረት በክልሉ ውስጥ ተቋቁመው በመሥራት ላይ ያሉ የህብረት ሥራ ማህበራት በዚህ አዋጅ መሠረት እንደገና ይደራጃሉ፣

**61. Supplying Information**

Every society shall have the obligation to transmit information to the appropriate authority about the activities it performs.

**62. Depositing of this Proclamation, Regulations and the By-Law**

Every society shall deposit at its address copies of this proclamation, the Regulations and the by-laws, to be accessible free of charge.

**63. Duty to Cooperate**

Any person shall have an obligation to cooperate for full implementation of the provisions asated in this proclamation.

**64. Repealed and Inapplicable Laws**

1. The Cooperative Society Establishment proclamation No. 134/2006 is repealed with this proclamation;
2. Any law, regulation, directives, customary practice which is inconsistent with this proclamation, shall not be applicable on matters provided in this proclamation.

**65. Transitory Provisions**

1. The Cooperative societies which have been established, in accordance with proclamation No.138/1978 and 85/1994 operating in the Region, shall be re-established, pursuant to this proclamation.

2. በፌዴራሉ መንግስት የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 /እንደተሻሻለ/ እና በክልሉ የኅ/ስራ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 134/98 መሠረት በክልሉ ውስጥ ተቋቁመው በመሥራት ላይ ያሉ የህብረት ሥራ ማህበራት በዚህ አዋጅ መሠረት እንደተቋቋሙ ተቆጥረው ሥራቸውን ያከናውናሉ፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተጠቀሱት ማህበራት እንደገና ተደራጅተው አግባብ ባለው ባለስልጣን እስኪመዘገቡ ድረስ የነበራቸውን ህጋዊ ሰውነት እንደያዙ ስራቸውን ይቀጥላሉ፡፡

## 66. ደንቦችንና መመሪያዎችን የማውጣት ስልጣን

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የሚረዱ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፤
2. አግባብ ያለው ባለሥልጣን ይህንን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች በሚገባ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## 67. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ-ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር

ጥቅምት 28 ቀን 2007 ዓ/ም

ገዱ እንዳርጋቸው

የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዚዳንት



2. Cooperative societies that have been established in accordance with the Federal State Cooperative Societies Establishment Proclamation No.147/1998 /as revised/; and, the Regional Cooperative Societies Establishment Proclamation No.134/2006, operating in the Region, Shall perform their activities as established, pursuant to this proclamation.
3. The societies indicated in sub-Article /1/ of this Article shall continue their operations holding their previous juridical personalities until they are reorganized and registered by the appropriate authority.

## 66. Power to Issue Regulations and Directives

1. The Regional Administrative Council may issue Regulations for the implementation of this proclamation.
2. The appropriate authority may issue directives that are necessary for the proper implementation of this proclamation and regulations issued with this proclamation, pursuant to this proclamation.

## 67. Effective Date

This proclamation shall come into force as of the date of publication in the Zikre -Hig Gazzettee of the Regional Government.

**Done at Bahir Dar,**

**This 7th day of November,2014**

**Gedu Andargachew**

**President of the Amhara National Region**